# ዜና ቤተ ክርስቲያን

ሠናይ እገሪሆሙ ለእለ ይዜንዉ ሠናየ ዜና፡፡

ዘኢትዮጵያ

መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው፡፡

ይህ ጋዜጣችን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት፣ ሥርዓትና ባሕል፣ ታሪክና ዜና የሚያትም ስለሆነ ዜና ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ተሠየመ፡፡

| 64ኛ ዓመት ቊ. 118 | የካቲትና መጋቢት 2017 ዓ.ም | የጋዜጣው ዋጋ 40..00 ብር | ለውጭ ሀገር እጥፍ ይሆናል | ☎ 550099 Ext.47 ✉ 1283 |
|---|---|---|---|---|

# የቅዱስ ፓትርያርኩ ፲፪ኛ ዓመት በዓለ ሢመት በድምቀት ተከበረ



የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት 12ኛ ዓመት በዓለ ሢመት የካቲት 24 ቀን 2017 ዓ.ም በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ተከብሮ ዋለ።

**ቅዱስ ፓትርያርኩ በዓሉን በተመለከተ አባታዊ መልእት አስተላልፈዋል የቅዱነታቸው መልእክት እነሆ**

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን፣

- ❐ ብፁዕ አቡነ አብርሃም የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ የባሕርዳር እና የሰሜን ጎጃም አህጉረ ስብከት ሊቀጳጳስ፣
- ❐ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት፣
- ❐ ክቡራን ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥል ጣናት፣
- ❐ ክቡራን ኣምባሳደሮችና የኮር ዲፕሎማቶች፣
- ❐ የተከበራችሁ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት የየመምሪያውና ድርጅት ኃላፊዎች፣
- ❐ የተከበራችሁ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች፣
- ❐ የተከበራችሁ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣
- ❐ የተከበራችሁ የገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች፣
- ❐ የተከበራችሁ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፤
- ❐ የተወደዳችሁ የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች፣

በአጠቃላይ በዚህ የቤተ ክርስቲያናችን በዓል የተገኛችሁ ካህናት፣ ምእመናንና ምእመናንት!

ከሁሉ በፊት ለመላው ውሉደ ክህነትና ሕዝበ ክርስቲያን እግዚአብሔር እንኳን ለዐሥራ ሁለተኛው ዓመት በዓለ ሢመተ ክህነት አደረሳችሁ እንላለን፡-

"አአኰተከ አባ እግዚአ ሰማያት ወምድር እስመ ኃባእኮ ለዝንቱ እምጠቢባን ወእማእምራን ወከሠትኮ ለሕፃናት እወ አባ እስመ ከማሁ ኮነ ሥምረትከ በቅድሜከ፡- የሰማይና የምድር ጌታ ኣባት ሆይ! ይህንን ከጥበ በኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለገለጥህላቸው ኣመሰግንሃለሁ፤ ኣዎን አባት ሆይ! ፈቃድህ በፊትህ እንዲህ ሆኖአልና" . (ማቴ.፲፩÷፳፭-፳፮)፤

ይህ የጌታችን የአምላካችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርተ ወንጌል ነው፤ ጌታችን በዚህ ኣስተምህሮው የሰማዩና የምድሩ ጌታና አባት ፈቃድ ምን እንደሆነ በግልጽ አስቀምጦልናል፡፡

ይኸውም የእግዚአብሔር ፈቃድ፣ የመንግሥተ እግዚአብሔርን ምሥጢር ማለትም ኢየሱስ ክርስቶስን የማወቅ ዕድል፣ እናውቃለን እንራቀቃለን ከሚሉ ጥበበኞችና አስተዋዮች መሰወር፤ በአንጻሩ ደግሞ እንደ ሕፃናት የዋሃንና ንጹሓን ለሆኑ ምእመናን መገለጽ እንደሆነ ነው፡፡

ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ የማይናወጥ ፈቃድ ነው፤ ትልቁ የእግዚአብሔር ጥበብና ምስጢር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ኣበክሮ ይነግረናል፡፡

ወደ ገጽ 3 ዞሯል ➩

## በውስጥ ገጾች


- ከቀደምት መጣጥፎች
- አጫጭር ዜናዎች
- የመጽሐፍ ዳሰሳ
- የቱን ትቼ የቱን ልጻፍ
- ስብከተ ወንጌል በዘመናት
- ዐሥራ ሦስቱ ሕማማተ መስቀል
- ክብረ ቅዱሳን

## ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ

**በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ሥር እየታተመ በየወሩ የሚወጣ**

**ዋና አዘጋጅ፡- መምህር ማርቆስ ተበቃ**

**ፎቶ ግራፈር፡- መልአከ ሰላም አባ ኪሮስ ወልደአብ አርታእያን**

**❍ መ/ሰላም አባ ሐዲስ ተሰማ**


### (ርእሰ አንቀጽ)

# ቀጣዩ የቤተ ክርስቲያን መንገድ መሪ ዕቅድ

ቤተ ክርስቲያናችን በየዘመናቱ የሚሱ ነገሥታት አንዱ መልካም አንዱ ግፍ ሲያጸ ናባት እንደመጣች ታሪክ ይመሰክራል፡፡ በእርግጥ ከጥንትም እንደምንረዳው ዓላዊ ንጉሥ ሲነሳ አብያተ ክርስቲያናት ይትአጸዋ፤ አማኝ ንጉሥ ሲነሳ አብያተ ክርስቲያናት ይትረሃዋ እያሉ ቤተ ክርስቲያን እስካሁኑ ዘመን ደርሳለች፡፡

እዚህ ለመድረሷ ምንም እንኳ የመንፈስ ቅዱስ ጥባቆት ባይለያትም በየጊዜው የሚመ ጣውን ፈተናና ተግዳሮት አልፋ በተደራጀ መልኩ ለመቀጠሏ ግን በየዘመናቱ የነበሩ አባቶቻችን ጊዜውን የዋጀ ተቋማዊ አሠራር በመዘርጋታቸው ነው፡፡

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አርቆ ዘአሳቢነት ዘመኑን የዋጀ የሰበካ ባይመሠርቱ ኖሮ በአሁኑ ሰዓት የቤተ ክርስቲያናን አቅምና ጉልበት በዚህ ደረጃ ይገኝ ነበር ወይ ብለን ብንጠይቅ በእርግጠኝነት አይሆንም ነበር ብለን አፋችን ሞልተን እንናገራለን፡፡

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለሰንበት ትምህርት ቤት ትኩረት ባይሰጡ ኖሮስ ትውልዱ ዛሬ በዚህ ልክ እናገኘው ነበር ወይ ብለን ስንጠይቅ ተመሳሳይ ምላሽ ነው የሚኖረው፡፡

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ካህናት ተጨማሪ ዘመናዊው ትምህርት እንዲማሩ ይገፋፉ የነበረውስ መጪው ዘመን ከባድ እንደሚሆንባቸው አርቀው በመመከል ከታቸው አልነበረምን፡፡

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ አብያተ ክርስቲያናት የልማት ተቋማት እንዲያ ስፋፉ የለፉት ዛሬ ያለውን ኢኮኖሚያዊ ስልት ቤተ ክርስቲያንን እንደሚፈትናት ተገንዝበው አልነበረምን፡፡

በቅዱሳን ፓትርያኮች አንቀጽ ተናገርን እንጂ ቀደምት አባቶቻችን ቤተ ክርስቲያንን ለማሻገር ያደረጓቸው ጥረቶች ተደማምረው ለዚህ ዘመን አድረሷታል፡፡ በአሁን ዘመን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ የምትመራው ቤተ ክርስቲያንም ለቀጣዩ ትውልድ እድትደርስ ለማስቻል አባቶቻችን ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

ለዚህም አገልጋይ ካህናትንና ምእመናንን የሚያስተረሳስር የአሥር ዓመት መሪ ዕቀድ በማኅልበት ወደ ተግባር ገብተዋል፡፡ ይህም እየተረቀዛቀዘ ለመጣው የዓሥራት በኩራት ገቢ ከመተካት አልፎ ንትርክና ጭቅጭቅ እየፈጠረ ለሚገኘውም የሰበካ ጉባኤ ፐርሰንት ገቢ መተኪያ የሚሆን ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያንም መጪውን ዘመን በኢኮኖሚ እና በቴክኖሎጂ ካልቀደመች አገል ግሎቷን ለማስቀጠል አዳጋች እንደሚሆን የገመቱት አባቶቻችን ይህን መሪ ዕቀድ በባለሙያ አስጠንተው መዋቅራዊ በማድረግ በመላው አህጉረ ስብከት ተግባራዊ እያደረጉት ይገኛሉ፡፡

እናም ቤተ ክርስቲያንን ከመጭው ዘመን ጋር የሚያገናኘው ይህ ዕቅድ ተግባራዊ እንዲደረግ የሁሉም ኦርቶዶክሳዊ ሓላፊነትና ግዴታ መሆን ይኖርበታል፡፡

ጥንት አባቶቻችን የሰበካ ጉባኤን ለማቋቋም ሲንቀሳቀሱ ጠቀሜታውን ያልተረዱ አገልገዮችና ምእመናን ድንጋይ ይወረውሩባቸው እንደነበርና በዚህም በርካቶች እንደሚጸጸቱ ይናገራሉ፡፡

ይህ የመሪ ዕቅድ ተግባራዊ እንዳይሆን እንቅፋት የሚፈጥሩ አካላት አይጠፉምና የወደ ፊቷን ቤተ ክርስቲያንን በመመልከት ለተግባራዊነቱ ሁሉም የበኩሉን መወጣት ይገባዋል፡፡

# ከቀደምት መጣጥፎች

## ስብከተ ወንጌል ለቤተ ክርስቲያን የደም ሥር ነው

ላንድ ብሔር ዕድገታዊ ተስፋ ሕዝባዊ ዕደገቱ የሚለካው በትምህርት ፋና ሲያንጸባርቅ በልዩ ልዩ የማምረቻ መሣሪያዎችና በሠለጠኑ የማምረቻ ኃይሎች ሲበለጽግ መሆኑ አይካድም፡፡ በዚሁ አኳያ ለቤተ ክርስቲያንም ዕድገት ያመምረቻ መሣሪያ ስብከተ ወንጌል እንደሆነ አጠራጣሪ አይሆንም፡፡

ጥንትም በሐዋርያት አሁንም ባለንበት ዘመን ምእመናንን በስብከተ ወንጌል እያሰ ባሰበና እያደራጀ በመንፈሳዊና በሥጋዊ ብልጽግና ረገድ ስብከተ ወንጌል ለቤተ ክርስ ቲያን ሕዋሳት የደም ሥርና መጋቤ ሕይወት እንደሆነ ሌላ አሻሚ ነገር አይኖረውም፡፡ አሌም እንዳይባልበት ሩቅ ሳንኼድ የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ መንፈሳዊ ሰበካ ጉባኤ የተፋጠነ ርምጃ የቅርብ አስረጂ ነው፡፡

ባለፈው ዓመት ግንቦት ፳፬ ቀን ፳፭ ዓ/ም በመንበረ ፓትርያርክ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ የመጀመሪያው የመንበረ ፓትርያክ አጠቃላይ መንፈሳዊ ሰበካ ጉባኤ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት በዘመናዊ ይዘት ከምንም ጊዜም ለየት ያለ ልማታዊ መሠረት መጣሉ ሲገመገም ጊዜው ሩቅ አይሆንም፡፡ ደግሞ አሁን ግንቦት ፲፬ ቀን ፳፮ ዓ/ም ለ፪ኛ ጊዜ የሚካኼደው (የተካኼደው) ፪ኛው የመንበረ ፓትርያክ አጠቃላይ መንፈሳዊ ሰበካ ጉባኤ ታሪካዊ መወቅሩ በተግባር እየታየ ነው፡፡

በ፳፮ ዓ/ም በ፩ኛና በ፪ኛ የስብከተ ወንወጌል ሥምሪት ሪፖርት እንደ ተገመተው በየሀገረ ስብከቱ ከገጠር እስከ ከተማ የተደረገው እንቅስቃሴ ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት የሕይወት መሰላል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህም ማለት ሥምሪቱ በመጀመሪያ ደረጃ ትኩረት የጣለበት ሰበካ ጉባኤ ባልተቋቋመበት ስፍራ ሰበካ ጉባኤን በማቋቋምና የተቋቋሙትንም በማጠናከርና ለኢትዮጵያ የታሪክ ዓይን የሆኑትን ጥንታውያንና ታሪካውያን ቅርሶችን በዘመናዊ ዘዴ በማስጠበቅ ነው ፡፡

ይህ አንዱ ሲሆን በሌላ በኩልም ከቋጥኝ በተፈለፈሉ የአብያተ ክርስቲያን ቱሪስታዊ ገቢዎችን፣ የሰበካ ጉባኤን አስተዋፅኦና ከስእለት እስከ ጠበለ ጠበላት ያለውን ልዩ ልዩ ገቢ በሁኔታው ቅጡ ጠፍቶ ሲኖር የነበረውን አሁን ግን የቅጽ ይዞታ እንዲረውና አቋሙ በቅጹ እንዲለካ መደረጉ ነው፡፡ ሥምሪቱ በዚህ ብቻ ሳይገታ የነገይቱን ቤተ ክርስቲያን እንዲረከብ ተስፋ የተጣበትን የሰንበት ት/ቤት አቋም በማስፋፋት በኩል ከመንብ'ኙቱም ሌላ ጥንትም ሆነ አሁን አንገብጋቢ ጥያቄነት ያለውን በችግር አንጻር የተበታተኑትን መምህራንን ማሰባሰብና የደሞዛቸውን ዕድገት በአካባቢው የምጣኔ ሀብት አንጻር ማሻሻልና ክብካቤ እንዲደረግላቸው ማድረግ ታላቅ ብሥራት ነው፡፡ እየቀደሱ መማ ምረት እያመረቱ መቀደስ እንዲቻል ካህናቱን በልማት አንጻር እንዲሠማሩ የልማት ፈር ማስያዝ ፣ የታሪኩ አኩሪነት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ አብያተ ክርስቲያናትም እንደሚሆን የተጣለበት ተስፋ በቀላሉ የሚገመት አይ ደለም ፡፡

በመሠረቱ እንደተገለጸው ይህ ዘመናዊ አሠራርን የተመለከተ ልማታዊና ትምህ ርታዊ እንቅስቃሴ በማንም በማን አደልም መሠረታዊ ትኩረቱ በስብከተ ወንጌል ብቻ እንደሆነ ታሪክ አይከደውም ፡፡

ከዚህም አልፎ ተርፎ በስብከተ ወንጌል ሥምሪት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መስፋፋትና ልማታዊ ዕድገት ከአህጉረ አፍሪቃ እስከ አውሮፓ እያንጸባረቀ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊት ኦርቶዶ ክሳዊት ቤተ ክርስቲያን በተባሉት አህጉራት ሁሉ ቤተ ክርስቲያን በመተከልና ሰባክያነ ወንጌልን በመላክ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዓለም አቀፍ አብያተ ክርስቲያናት ደረጃ ህልውናዋ እያበበ ይታያል፡፡

በእርግጥም እንደ ተባለው ስብከተ ወንጌል ሊተማመኑበት የሚገባ የእግዚአብሔር ረቂቅ ኃይል ነው፡፡ ረቂቅ የሆነው የስብከተ ወንጌል መንፈሳዊ ሰይፍ በረቂቃን አጋንንት ላይ በሚብለጨለጭበት ብሔር የእግዚአብሔር መንፈስ ረድኤት በየጽላቱ ፣ በየጠበላቱ ፣ በየካህናቱ እያደረ ተአምራት ፣ መንክራት ፣ ኃይላት ማለትም ድውይን የመፈወስ ፣ አጋንንትን የማሶጣት ፣ ሙታንን የማስነሣት ሥልጣን ይሰጣል፡፡ ይህም የመንፈሳዊ ሰይፍ ትጥቅ የሚሰጠው ለማስተማርና ሥራ ለመሥራት ሳይሆን በማባበልና በመደለል ስለፍቅረ ንዋይ ከከተማ እስከ ገጠር ለቀደመ ለሮጠ አስመሳይ ሰባኬ ወንጌል አይደልም ሥራ ለሚሠራና ክርስቶስን እስከ ሞት በሚገባ ለሚያገለግል መንፈሳዊ አርበኛ ነው እንጂ እንላለን፡፡

**ዜና ቤተ ክርስቲያን ዘኢትዮጵያ ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፳፮ ዓ/ም**

ከገጽ 1 የዞረ

## የቅዱስነታቸው መልእክት ....

እግዚብሔር አምላካችን ዓለም ይህንን ምስጢርና ጥበብ ኣውቆ አምኖና ተቀብሎ መጻኢ ዕድሉን እንዲያሳምር ይጐተጉታል፡፡ ጌታችን በአካለ ሥጋ በዚህ ዓለም ተገልጾ በሚያስተምርበት ጊዜ ይህ ጥበብና ምስጢር የተሰወረባቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ነበሩ፡፡ ምስጢሩ ሊሰወርባቸው የቻለው በጥበባ ቸውና በዕውቀታቸው የመመካት ችግር ስለነበራቸው እንደሆነ ቃሉ ይጠቁማል፤

**ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ክቡራን የበዓሉ ተሳታፊዎች!**

መቼም እኛ ሰዎች በሥልጣን፣ ወይም በዕውቀት ወይም ደግሞ በሀብት በአጠገባችን ካሉ ሰዎች የተሻልን ነን ብለን ስናስብ የት ዕቢት መንፈስ ይወረናል፤ ትዕቢት ደግሞ እውነትንና ዓቅማችንን እንዳናውቅ ኣእምሮ ኣችንን በመሸበብ ለሰዎች ሓሳብና ሰብእና አክብሮት እንዳንሰጥ እንደሚያደርገን የታወቀ ነው፡፡ በወቅቱ ጠቢባንና አስተዋዮች ነን የሚሉ የአይሁድ አለቆችና መሪዎችም በዚህ ደካማ ሰብኣዊ ጠባያቸው በራሳቸው ዕው ቀት ስለተማመኑ የእግዚብሔር ጥበብና ምሥ ጢር የሆነውን ክርስቶስን ለማወቅና ለመቀ በል ዝንባሌውና ፍላጎት ኣልነበራ ቸውም፡፡ በመሆኑም ፍላጎት ላለው ጨምሮ መስጠት ለሌለው ግን ያለውንም መንሣት ጠባዩ የሆነ እግዚአብሔር አምላክ የነበራቸውንም ጨርሶ ሰውሮባቸዋል፤ ምክንያቱም የእግዚ አብሔር ፈቃድ ምስጢሩን ከትዕቢተኞች መሰወር ለትሑታን ግን መግለጽ በመሆኑ ነው፤ በጌታችን ኣስተምህሮ እዚህ ላይ ሕፃናት እየተባሉ ያሉ የእሱን መሲሕነት አውቀው ኣምነውና ተቀብለው ከእርሱ ጋር ይጓዙ የነበሩ አይሁዳውያን ተከታዮቹን ነው፤ እነሱ በቅንነትና በትሕትና እንዲሁም የዕውቀት ሕፃናት እንደሆኑ አውቀው የበለጠ ዕውቀትን ከሱ ለማግኘት ፍላጎት ስለነበ ራቸው እሱነቱን ገለጸላቸው፤ ይህ የእግዚ አብሔር ፈቃድ ጥንትም ሆነ ዛሬ የነበረ ያለና የማይለወጥ ቀዋሚ ፈቃዱ ነው፤ ከዚህ አንጻር ዛሬም ቢሆን ጥበቡን ከትዕቢተኞች ይሰው ራል፤ ለሕፃናት አማንያን ግን ይገልጻል፤

***ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ክቡራን የበዓሉ ተሳታፊዎች!***

ዛሬም እንደቀድሞው ዓለም በዕውቀቷ በሥልጣንዋና በሀብቷ እየተመካች ለእግዚ አብሔር ቃል ጆሮ ዳባልበስ ስላለች ምስጢ ሩና ጥበቡ ተሰውሮባታል፤ ከክርስቶስ ጥበብነ ትና ምስጢርነት ይልቅ ምርጫዋ የጨለማው ገዥ ጠባያትን መቀበልና ማስፋፋት ምር ጫዋ ሆኖአል፤ ለዚህም ተግባርዋ የተመሳሳይ ፆታ ነውረ ኃጢኣትና የአምልኮ ባዕድ እምነቶች ሕጋዊ ዕውቅና እንዲያገኙ የምታደርጋቸው ጥረቶችንና ለኔ ለኔ በሚል የስግብግብ አመለ ካከት የምታካ ሂዳቸው ኣውዳሚ ጦርነቶች ዋና ዋና ማሳያዎች ሆነው ይገኛሉ፤ የሰው ልጅም ከነዚህ እኩያት ተግባራት በነፍሱ ብቻ ሳይሆን በሥጋዊ ኑሮውም ቢሆን ከጉዳት በቀር ቅንጣት ታህል ጥቅም ማግኘት እንደ ማይችል ማወቅ ተስኖታል፤ እግዚአብሔር ግን የዚህ ዓለም ጥበብ ሞኝነት እንደሆነ አጠንክሮ ነግሮናል፤ ታድያ የዓለም ጥበብና ዕውቀት በእግዚአብሔር ፊት ይህን ያህል ሞኝነት ከሆነ እኛ ሕፃናት ኣማንያን ምን እየሰራን ነው የሚለው ተስእሎት የዚህ ዕለት ኣንኳር ጥያቄአችን ሊሆን ይገባል፤



ከሁሉ በፊት እግዚብሔር ይህንን የክርስቶስን ምስጢርነት የገለጸልን ሕፃናት ሆነን በመገኘታችን እንደሆነ ከእርሱ የበለጠ መስካሪ ኣያስፈልገንምና እሱን ኣጥብቀን እንጨብጥ፤ ቀጥሎም በዚህ ቅዱስ ፈቃዱ ሕፃናት የሆነው እኛን በልዩ ምርጫው ፓትርያርክ፣ ሊቀ ጳጳስ፣ ኤጲስ ቆኦስ፣ ቀሲስ፣ ዲያቆን፣ ምእመንና ማእምንት በሚል ሰይሞ በመንግሥቱ ውስጥ እንድናገለግል የተቀበለን መሆኑን ለአፍታ እንኳ አንዘንጋ፡፡



***ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፣ ክቡራን የበዓሉ ተሳታፊዎች !***

እግዚአብሐር እኛ ካህናትን በጎቹን በን ጽህና እና በቅድስና እንድንጠብቅ፣ በምድር ላይ ሰላምና ሰላም ብቻ እንድናውጅ፣ ፍትሕ ርትዕ እንዳይዛባ እንድንመክር፣ ኣንድነትና እኩልነት እንዳንነጣጥል፣ ፍቅርና ይቅርታ እንዳይቀዘቅዝ ሌት ተቀን እንድናስተምር የሰላም ወንጌልን አስጨብጦናል፤ ከሁሉ በላይ ደግሞ በቤቱ ቤተኛ ሆነን እንድናዝና እንድናዝዝ ኣድርጎናል፤ ታድያ በቤቱ ሆነን የምንሰጠው አገልግሎት ለባለቤቱ የሚመጥን እንዲሆን ያስፈልጋል፤ ተገልጋዮች ምእመ ናንም በአገልግሎታችን ደስተኞች መሆና ቸውን ማረጋገጥ ኣለብን፤ ሁላችንም ውሉደ ክህነት በውል ልንገነዘበው የሚገባ ዓቢይ ቁም ነገር፣ ኣሁን ባለን ቁመና ቤተ ክርስቲ ያንን በሚፈለገው ደረጃ ወደ ቀጣዩ ትውልድ በአስተማማኝ ሁኔታ ማሸጋገር ያዳግታል፤ ላለንበት ዘመን የማይመጥኑ ብዙ የስራ ኣፈጻ ጸሞች አሉብን፤ እነዚህን ከምር ኣውቀን በማስተካከል ወደ ተሻለ የስራ አፈጻጸም ካልተሻገርን በምድርም፣ በሰማይም፣ በታሪ ክም፣ በኅሊናም ተወቃሽ ከመሆን ኣናመ ልጥም፤ ከላይ ጀምሮ እስከታች ያለው ውሉደ ክህነት ከዚያም መላው ሕዝበ ክርስቲያን በዚህ ላይ የበኩሉን ኃላፊነት ለመወጣት በርትቶ እንዲሰራ ያስፈልጋል፤

***በመጨረሻም፤***

እኛ የሃይማኖት አገልጋዮች ሃይማኖትን ስንጠብቅ ሕዝብን ይዘን ነው፤ ያለ ሕዝብ ሃይማኖት ይኖራል ተብሎ አይታሰብም፤ የሕዝብም መኖር ያለሰላም አይታሰብም፤ ሃይማኖት እንዲኖር ሕዝብ መኖር አለበት፤ ሕዝብ እንዲኖር ሰላም መኖር አለበት፣ እነዚህ የማይነጣጠሉ ናቸው፤ አሁን ባለንበት ጊዜ ግን የሁሉም ፈተና በዝቶአል፤ ስለሆነም በሕ ዝቦች አንድነትና ሰላም፣ በፍትሕና እኩልነት ላይ አጥብቀን እንድናስተምር የወቅቱ ኣባታዊ ጥሪያችንና መልእክታችን ነው፡፡

**እግዚአብሔር መልካም በዓለ ሢመተ ክህነት ያድርግልን!**
**“እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ”**
**ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን**
**አባ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ**
**ሊቀ ጳጳስ ዘአኵስም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት**
**የካቲት 24 ቀን 2017 ዓ.ም**
**አዲስ አበባ ኢትዮጵያ**

# ብፁዕ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ፲፪ኛ ዓመት በዓለ ሢመትን አስመልክቶ መልእክት አስተላለፉ

ብፁዕ አቡነ አብርሃም የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ፣ የባሕርዳር የሰሜን ጎጃም አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ያስተላለፉት መልእክት::

***አእኵቶ ወእሴብሖ ወእሌዕሎ ለንጉሠ ስብሐት እስመ ጽድቅ ቃሉ እሙን ነገሩ ወርቱዕ ኩሉ ፍናዊሁ::***

***የክብር ንጉሥን ፈጽመ አመሰግነዋለሁ:: ቃሉ እውነት ነገሩ የታመነ መንገዱ ሁሉ የቀና ነውና !! (ቅዱስ ያሬድ)***

**ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን**

ዛሬ የምናከብረው የቅዱስነትዎ በዓለ ሢመት የቅድስት ቤተ ክርስቲያን በዓል ነው:: በእሉን ለማክበር ያበቃን ምክንያቱም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ ቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ከዚህ ደረጃ ለመድረስ የአበው ጸሎት፣ የነገሥታት ቁርጥ ውሳኔ፣ በወቅቱ በነበሩ ሊቃውንት በሀገራችን ሊቀ ጳጳስ ይሹምልን በሀገራችን ቋንቋ እንግር በሚል በመንፈሳዊ ቅናትና ጥረት የተገኘ ውጤት ነው:: በእውነትና በታመነ ነገር መን ገዱን ተከትለው በአስገኙት ታሪካዊ፣ ሃይማ ኖታዊና ቀኖናዊ መሠረትም ላይ ቆመን ነው::

ነገር ከሥሩ ውኃ ከጥሩ እንዲሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብፁዓን አበው ሐዋርያትን "ሑሩ ሐሩ ወመሐሩ ኩሎ አሕዛበ" ብሎ ዓለምን ዞረው እንዲያስተምሩ ሲሾማቸው ቀለም ዘር ቋንቋ የሚባሉ ስም አጠራሮች ቦታ አልነበራቸውም:: በእምነት ሳይሆን በሥርዓት ስለቀደሙን አባት እንዲሾሙልን የጠየቅ ናቸው ወገኖቻችን ግን የጌታችንን ቃል ወደጎን ብለው በሥርዋፅ አስገቡተው "ወሰብአ ኢትዮ ጵያሰ ኢይሢሙ ሊቀ ላዕሌሆሙ እማእ ምራኒሆሙ፤ የኢትዮጵያ ሰዎች ከዐዋቂዎ ቻቸው ሊቀጳጳስ በራሳ ቸው አይሹሙ::" ብለው በዐራተኛው አንቀጽ ወስነው ለዘመናት የቅኝ ተገዥዎች አድርገውን ነበር:: ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፬፥፶

በዚህ አንቀጽ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ታሥራ ትኖር ነበር:: ይህንን ልብ ያሉ ሊቃውንት አንቀጹን ሃይማኖታዊ ወይስ ፖለቲካዊ በማለት ሲወዛ ገቡ ዓመታትን አሳልፈዋል::

ይህንን አንቀጽ የቤተ ክርስቲያን ሊቃ ውንት በተለያየ መልኩ ገልጸውታል:: ተቃው መውታል:: አንዳንዶች "ቀንበር ማጥበቂያ አንቀጽ" ሲሉ ይጠሩታል:: የኢትዮጵያ ኦርቶ ዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም እስከ መጀ መሪያው ፓትርያርክ ድረስ በዚህ ቀንበር ታንቃና ተይዛ የራሷ ቅዱስ ሲኖዶስ፣ የራሷ ቅዱስ ፓትርያርክ የራሷ አበው ሊቃነ ጳጳሳት ሳይኖራት ዘመናት ተፈራርቀዋል::

ከፊሎች የፍትሐ ነገሥት ሊቃውንት ደግሞ አንቀጹን እንደተለመደው አንድም ብለው ሳይተረጉሙ "ይህ አውነት አይደ ለም!" እያሉ በተቃውሞ አልፈውታል::

የሃገርን ክብርና ፍቅር ከሃይማኖት ጋር አጣምረው የያዙ ዐይናማ ሊቃውንት ግን "ይህ አንቀጽ በሥርዋጽ የገባ አንቀጽ ነው" በማለት እንደሚገልጹት የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ:: ከሊቃውንቱ ጎን ለጎን ነገሥ ታቱም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በራሷ አባቶች እንድትመራ መንፈስ ቅዱስ አነሣሥ ቷቸው የራሳቸውን ከፍተኛ ጥረት አድር ገዋል:: ከነገሥታቱ ቀዳሚው በ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩት ንጉሥ ሐርቤ (ቅዱስ ገብረ ማርያም) ነበሩ:: በዘመኑ ከግብጽ ተሹመው የመጡት ሊቀጳጳስ አባ ሚካኤል ይባሉ እንደነበር ታሪክ ይነግረናል::



ንጉሡም "የኢትዮጵያ ምእመናን ብዙ ናቸው:: የሀገሬም መልክአ ምድር ሰፊ ነው:: ዳሩ ግን ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ በቋን ቋቸው ወንጌል የሚያስተምራቸው ኢትዮ ጵያዊ ሐዋርያ የላቸውም:: ቤተ ክርስቲያን ሲያንጹ ባርኮ የሚያከብርላቸው ሊቀ ጳጳስ የለም:: ሌላው ቀርቶ በሀገራቸው ቋንቋ ቀድሶ የሚያቆርባቸው ኢትዮጵያዊ ጳጳስ የላቸውምና ጳጳሳት ይሾምላቸው" ብለው ሐሳብ አቀረቡ:: ግብጻዊውም አባ ሚካኤ ልም ይህን ውሳኔ ብቻዬን የምወስነው አይ ደለም:: ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ልምከርበት ልዝከርበት" ብለው ወደ ሀገራ ቸው ወደ ግብጽ ወረዱ:: ንጉሥ ሐርቤም (ቅዱስ ገብረ ማርያም) መልካም ዜና የሆነ ውን የቤተ ክርስቲያንን የምሥራች ሲጠብቁ በወቅቱ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ፓትር ያርክ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ገብር ኤል የፍትሐ ነገሥቱን ሥርዋጽ ጠቅሰው፣ ቀንበር ማጥበቂያውን አጥብቀው "ሠለስቱ ምእት በኒቅያ ጉባኤ የደነገጉት አስመስለው አሳከለው" ይህማ የሠለስቱ ምእትን ትእዛዝ መተላለፍ ነው" ብለው ከለከሏቸውም:: በመከልከል ብቻ አላቆሙም:: በጊዜ ገጠ መኝ በኢትዮጵያ የተከሰተውን የረሓብና ድርቅ ዘመን ጠቅሰው የኢትዮጵያው ንጉሥ ሐርቤ (ቅዱስ ገብረ ማርያም) ጳጳስ ሊሾም በመፈለጉ ጌታችን ተቆጥቶ በኢትዮጵያውያን ላይ ቸነፈር አወረደ:: ሰማይ ለጉመ:: ዝናም ከለከለ:: ጽኑ ረሓብ ኾነ:" የሚል መላምት ጨምረው ወደ ኢትዮጵያ ደብዳቤ ጻፉ:: ሕዝቡም እውነት መሰለው:: በዚህ ምክንያት የንጉሥ ሐርቤ ተምኔት ሳይሳካ ቀረ:: ዳሩ ግን ከንጉሥ ሐርቤ (ቅዱስ ገብረ ማርያም) በኋላ የነገሡ ነገሥታት ተስፋ አልቆ ረጡም:: ለምሳሌ አጼ ዐምደ ጽዮን በ1304 ለግብጹ መሪ ጥያቄ አቅርበው ነበር:: አል ኾነም:: አጼ ይሥሐቅም በ1423 ለነበረው የግብጽ መሪ ደብዳቤ ጽፈው ነበር:: መልሱ አልመ ጣላቸው:: አጼ ዘርዐ ያዕቆብም ለ1443 ዓ.ም. በጊዜው ለነበረው ሡልጣን ሐሳቡን አንሥተው ነበር:: ፍጻሜ አላገ ኘም:: ቀጥሎ አጼ እስክንድር በ1481 ዓ.ም. ደብዳቤ ቢጽፉ ጥያቄአቸው ቀና መልስ አግኝቶ ኢትዮጵያዊ ሊቀጳጳስ ሊሾም አልቻ ለም"፡ የአምስቱም ነገሥታት ድካም ፍሬ ሳያፈራ ቀረ:: ያም ሆኖ በየጊዜው የተነሡ ምሁራን በሐሳቡ ገፉበት:: የኢትዮጵያ መሪዎችም ተሳተፉበት::

በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደገና አጼ ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት ዐራተኛ የንጉሥ ሐርቤን (ቅዱስ ገብረ ማርያምን) ጥያቄ የመሰለ ተመሳሳይ ጥያቄ አቀረቡ:: የእስክን ድርያው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ግን ጥያቄውን ሙሉ በሙሉ ባይቀ በሉትም በኢትዮጵያውያን ፈንታ ከዚያው ከግብጽ ሦስት ኤጲስ ቆጶሳትና አንድ ሊቀ ጳጳስ ሹመው በአዲስ መልክ ላኩ:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ ግን እን ደገና እየገፋ መጥቶ ከንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከራስ ተፈሪ መኰንን ዘመን ደረሰ::



በንግሥተ ነገሥታት መሪነት፣ በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ ራስነት ነገሩ በጥልቅ ተያዘ:: በወቅቱ ራስ በኋላ ግርማዊ ቀዳማዊ የኾኑት አጼ ኀይለ ሥላሴ ባደረጉት ጥረት ለመጀሪያ ጊዜ በ1921 ዓ.ም. ዐራቱ ሊቃነ ጳጳሳት ግንቦት 25 ቀን በካይሮ ግብጽ ተሾሙ:: ያን ጊዜ ኢትዮጵያውያን "በአማን ተፈጸመ ፍሥሓሃ ለቤተ ክርስቲያን ዘኢት ዮጵያ" ብለው የሊቁን ቃል ተቀኙት:: ቤተ ክርስቲያንም በደስታ እግዚአብሔርን አመሰ ገነች:: ይሁን እንጂ አንድ ነገር ይቀር ነበር:: ይኸውም ሢመተ ፓትርክና የቅዱስ ሲኖዶስ ምሥረታ ነበር:: ከ1921 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1951 ዓ.ም. ፓትርያርክ አልነ በረም:: ግርማዊ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት አጼ ኀይለ ሥላሴ ግን እንደጀመሩ ይፈጽ ሙት ዘንድ የኢትዮጵያን ሊቃውንት ከዐ ራቱ ማእዘን ጠርተው በኢትዮጵያ ቅዱስ ሲኖዶስ እንዲኖር ዶግማውን ጠብቀው ቀኖናውን አጥንተው እንዲያቀርቡ በተሰ ጠው ውሳኔ መሠረት "ወሰብአ ኢትዮጵያሰ ኢይሢሙ ሊቀ ላዕሌሆሙ እማእምራ ኒሆሙ" ተብሎ የተጻፈው ተመረመረ:: ቃሉ በቁሙ የሠለስቱ ምእት ቃል ሳይሆን በሥር ዋጽ የገባ ቃል እንደሆነ ተረጋገጠ:: ይህ ቃል ኢትዮጵያ ለራሷ ሊቀጳጳስ እንዳይኖራት የብረት አጥር ሆኖ ተጋርዶባት ነበርና ተነቅሎ ወደቀ:: የተጋረደው የጨለማ መጋ ረጃም ተቀዶ በ1951 ዓ.ም. የመጀመሪያው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ተመርጠው ተሾሙ:: ኢትዮጵያውያንም በራሳቸው ፓትርያርክ አንብሮተ እድ ኤጲስ ቆጶስ፣ ጳጳስ፣ ሊቀ ጳጳስ እየተባሉ ይሾሙ ዘንድ እግዚአብሔር ፈቀደ::

አሁንም ኢትዮጵያውያን "በአማን ተፈ ጸመ ፍሥሓሃ ለቤተ ክርስቲያን ዘኢት ዮጵያ" ብለው ዘመሩ:: ከዚህ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን "አምስት ቅዱሳን ፓትር ያርኮች" ተሹመው በተሰጣቸው ጸጋ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የቤተ ክርስቲያንን ዶግማ ጠብቀው ቀኖናውን አክብረው ሕገ ቤተ ክርስቲያንና ቃለ ዐዋዲ ቀርጸው ምእመናን የቁሣርን ለቄሣር የእግዚአ ብሔርን ለእግዚአብሔር እንዲሰጡ እያስተማሩ የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት እያፋጠኑ ልማት እያለሙ ኑረው አረፍተ ዘመን ገትቷቸዋል::

በመሆኑም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ቅዱስ ነትዎን 6ኛ ቅዱስ ፓትርያርክ አድርጎ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በመንበሩ ሠይሞአል::

ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን አቡነ ማትያስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢት ዮጵያ ሊቀጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመ ንበረ ተክለ ሃይማኖት በታሪክ መነጽር ወደኋላ ተመ ልሰን በአክብሮ እንደተመለ ከትነው የቀድሞ ነገሥታት፣ አበው መነ ኰሳት፣ እንዲሁም ሊቃውንት በመንፈሳዊ ቅናት በብዙ ድካምና ውጣ ውረድ የተመ ሠረተ ቅዱስ ሲኖዶስ እና ፓትርክና እስከ ዛሬው ድረስ በእግዚአብሔር ቸርነት በአበው ዋላዊነት ወደፊት መሠረቱ ሳይናወጥ እንዲ ቀጥል ዘመኑን እየዋጀን የጠመ መውን እያቀናን የጐደለውን እየመላን የጠፋውን እየፈለግን በጾም በጸሎት እየተ ጋን መሄድ የግድ ይሆናል::

↳

ያን ጊዜ የቅዱስ ሲኖዶስ መሪ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ቅዱስ ሲኖዶ ስም በአንድ አቋም የእረኝነቱን ሥራ ተግቶ ይሠራል፡፡

ይሁን እንጂ ኖላዊነታችንን ረስተን ቤተ ክርስቲያንን ከመጠበቅ ይልቅ በተለያዩ ምክንያቶች ተጠምደን በጊዜው ባንጠቀ ምበት በተጋድሎ የተገኘው ቅዱስ ሲኖዶስ በመለ ያየት ከእጃችን ሊያመልጥ ይችላል፡፡ ያን ጊዜ ወገኖቻችን ድሮም ቢሆንኮ ሕግ ጥሰው ትእዛዝ ተላልፈው ነው እንጂ ለኢትዮ ጵያውያን ሊቀ ጳጳስ መሾም፣ ቅዱስ ሲኖዶስ ማቋቋም፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ አልነ በረም፡፡ ሕገ እግዚአብሔርን ተዳፍረው ነበረና ተበተኑ፡፡ ይህ ጸጋ የተሰጠ ለእኛ ብቻ ነው" ብለው ሊሳለቁብን ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የታሪክ ተወቃሽ እንዳንሆን በብዙ ድካም የተሰጠንን ጸጋ መጠበቅ የሁላችን ሐላፊነት መሆኑን ሳወሳ በታላቅ ትሕትና ነው፡፡

**ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን**

በፈቃደ እግዚአብሔር በዚህ ቅዱስ መንበር ከተሰየሙ ጀምሮ በጸሎትዎና በአመ ራርዎ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስ ቲያናችን ከፍተኛ ዕድገት አሳይታለች፣ ገቢዋ ከፍ በማለቱ የካህናት ኑሮ ተሻሽሏል፡፡ አልፎ ተርፎም ብዙ የሥራ መስኮች በመከፈ ታቸው በብዙ የሚቆጠሩ ወንድሞችና እኅ ቶች በየሙያቸው ተቀጥረው የቤተ ክርስ ቲያኒቱ ሠራተኞች ሁነዋል፡፡ ከአጥቢያ እስከ መንበረ ፓትርያርክ የተለያዩ የልማት አውታሮች ተዘርግተዋል፡፡ ቅድስት ኦርቶዶ ክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ዘመ ኑን ዋጅታ እምነቷንና ቀኖናዋን ጠብቃ ከዘመኑ ጋር መራመድ እንድትችል በመሪ ዕቅድ እንድትመራ ታላቅ መሠረት ጥለዋል፡፡ ኦርቶዶክሳውያን ልጆቿ በሚገኙበት በዓ ለም ዙሪያ በብዙ የሚቆጠሩ አብያተ ክርስ ቲያን ተተክለዋል፡፡

በተለያዩ አህጉረ ስብከቶች ኮሌጆችና የምስክር ጉባኤ ቤቶች ተስፋፍተዋል፡፡ በአጠ ቃላይ የዘመኑን ፈተና በመቋቋም በፈቃደ እግዚአብሔር ታሪክ የማይረሳቸው ሥራዎች በዘመንዎ ተከናውነዋል፡፡

**ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን**

ይህ ሁሉ የሆነው የኢትዮጵያ ኦርቶ ዶክስ ተወሕዶ ቤተ ክርስቲያን በራሷ ቅዱስ ፓትርያርክ ማለትም ቀኖናዋን ታሪኳን ባሕሏን በሚያውቁ ልጆቿ በመመራቷ ለብዙ ዘመናት ያልተሠሩ ሥራዎች ተሠር ተዋል፡፡ ምንጊዜም በጸሎት ተግቶ በትግ እስት ራስን ገዝቶ ፈቃደ እግዚአብሔርን የጠየቀ ሁሉ ተምኔቱ ይፈጸምለታል፡፡ የሚናገ ረውም ነገር ይታመንለታል፡፡ መንገዱ ምንም እንኳ ረጅምና አድካሚ ቢሆንም የቀና ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ሁሉ እንደ አባቶቼ "አዐኵቶ ወእሴብሖ ወአሌዕሎ ለንጉሠ ስብሐት እስመ ጽድቅ ቃለ እሙን ነገሩ ወርቱዕ ኵሉ ፍናዊሁ፤

የክብር ንጉሥን ፈጽሞ አመሰግነዋለሁ፡፡ ቃሉ እውነት ነገሩ የታመነ መንገዱ ሁሉ የቀና ነውና፡፡

የአባቶቻችን ጸሎትና ጥረት ድካምና አገልግሎት ተቀብሎ የፈጸመ ቅዱስ እግዚ አብሔር የተመሰገነ ይሁን እያልሁ በድጋሚ እንኳን ለ12ኛው በዓለ ሢመትዎ በሰላምና በጤና አደረሰዎ በማለት ቀሪ ዘመንዎ የጤና የሥራ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አንድነት የሚጠበቅበት የሀገራችን ሰላም የሚሰፍንበት ዘመን እንዲሆንልዎ መልካም ምኞቴን በታላቅ ትሕትና አቀርባለሁ፡፡

**የቅዱስነትዎ ቡራኬ ይድረሰኝ !!**

**አባ አብርሃም የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ፣ የባሕርዳር የሰሜን ጎጃም አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ**
**የካቲት 24 ቀን 2017 ዓ.ም.**

☞ ከገጽ 11 የዞረ

## ዜና ዕረፍት ....

ሮትና ፍቅር የተቸራቸው ታላቅ ምሁር ነበሩ። ከአጥቢያ እስከ መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ድረስ ለአበረከቱት አገል ግሎት ቤተ ክርስቲያን ምን ጊዜም ቢሆን ታስባቸዋለች።

በተለይ በተወለዱበት ቦታ በአንዳንድ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት በፈጸሙት በጎ ተግባር ለመቀደሻና ለክብረ በዓል የሚሆን ልብሰ ተክህኖ፥ የኅትመት ውጤቶች የሆኑ ታላላቅ መጻሕፍት፥ ጥላ፥ ዕጣን፥ ዘቢብ፥ ጧፍ፥ ሻማ የመሳሰሉትን በመላክ ከሰባት በላይ አብያተ ክርስቲያናትን ሲረዱ ኑረዋል። ለአንዳንድ የአብነት መምህራንም ከግል ገንዘባቸው ሲረዱ ቆይተዋል።





**ስለ ሊቀ አእላፍ ያዝዓለም ገሠሠ ከሊቃውንት ጉባኤ የተሰጠ ምስክርነት**

በእላ ክልኤቲ ትእዛዛት ተሰቅሉ ኦሪት ወነቢያት በማለት ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረን፡፡

ስለ ታላቁ ሊቅ ሊቀ አእላፍ የኔታ ያዝዓ ለም ገሠሠ በጉባኤ ሊቃውንት ከአባልነት እስከ ሰብሳቢነት በሚሠሩበት ጊዜ የሰማነ ውንና ያየነውን ለመመስከር ያህል፡-

ሊቀ አእላፍ የኔታ ያዝዓለም ገሠሠ ሊቃ ውንት ጉባኤን በሰብሳቢነት በሚመሩበት ጊዜ ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ የጸና ላቸው፥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በጢሞ ቴዎስ መልእክቱ፡- ***"ወገብረ እግዚአብሔርሰ ኢይትገአዝ አላ ከመ ሕፃን የዋህ ይከውን***




***ምስለ ኵሉ ወመምህረ ወመስተዓግሠ እም ኵሉ እኩይ -- የእግዚአብሔር አገልጋይ ግን የማይጣላ ከሁሉ ጋር እንደ ሕፃን የዋህ፥ ለማስተማር የሚበቃ፥ ክፉ ነገርንም ሁሉ የሚታገስ ይሆናል"*** (2ጢሞ. 2፥24) እንዳለ፥ ሊቀ አእላፍ ሊቅነትንና የአመራር ጥበብን ከደግነት አስተባብረው የያዙ፥ ሰውን በማንነቱ ሳይለዩ የሚያከብሩ፥ በአንደበ ታቸው ክፉ የማይናገሩ፥ ትንሽ ትልቅ ሳይሉ ሁሉንም በእኩል ዐይን የሚመለከቱ አባት ነበሩ፡፡

ክቡር ሊቀ አእላፍ ያዝዓለም ለሀገራቸ ውና ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸው ከፍተኛ ፍቅር የነበራቸው አባት ሲሆኑ፡- በጉባኤ ሊቃውንት የመሪነት ዘመናቸው የግእዙ መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድ ጥራዝ ተጠቃሎ እንዲታተም በጉባኤው ይደረግ በነበረው የዝግጅት ሥራ ጉባኤውን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበርንና ሌሎች አካ ላትን በማስተባበርና በማቀናጀት አጠቃላይ የሚፈለገው የሥራ ውጤት ተመዝግቦ ዛሬ በእጃችን ላይ የሚገኘው ሙሉው የግእዝ መጽሐፍ ቅዱስ ለቅድስት ቤተ ክርስ ቲያን ያበረከቱ ታላቅ መሪ ነበሩ፡፡

ክቡር ሊቀ አእላፍ ያዝ ዓለም ገሠሠ የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ተልዕኮ ውጤ ታማ እንዲሆን የነበራቸው ትጋትና ቀናዒነት፥ ተተኪ መሪዎችንም በተግባር ለመፍ ጠር የነበራቸው ተምሳሌ ትነትና ምሁራዊ አርዓያነ ታቸው ሁሉም የሚመሰክ ርላቸው ሐቅ ነው፡፡

በማኅበራዊ ሕይወታቸውም፡- የሁሉ አባ ትና መካሪ፥ እንዲሁም ታናሽ ታላቅ ሳይሉ ሰውን አክባሪነታቸው ሌላኛው አይረሴ መገለ ጫቸው ነበር፡፡

ክቡር ሊቀ አእላፍ ያዝዓለም ገሠሠ በዚህ ዓለም ሲኖሩ ሦስት ልጆችን አፍር ተዋው አንዱ በሞት ቢለይባቸውም፤ ሁለቱን ሴቶች ልጆቻቸውን አስተምረው ለቁም ነገር አድርሰው፥ ድረው፥ ኩለው የልጅ ልጆች ለማየት በቅተው እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ኑረዋል።

ክቡር ሊቀ አእላፍ ያዝዓለም ገሠሠ በጸና ሃይማኖት፥ በትዕግሥትና በጸሎት ተወስነው፥ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እየተቀበሉ እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ ከኖሩ በኋላ፤ በአደረባቸው የጤና እክል በሀገር ውስጥና በአሜሪካ ሀገር በሕክምና ሲረዱ ቆይተው፥ መጋቢት 24 ቀን 2017 ቀን ከዚህ ዓለም ድካም በ81 ዓመታቸው አርፈዋል።

ሥርዐተ ቀብራቸውም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፥ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፥ የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት የመምሪያና የድርጅት ኀላፊዎችና ሠራተኞች፥ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፥ ልጆቻቸውና ቤተሰቦቻቸው፥ ወዳጅ ዘመዶቻቸው በተገ ኙበት መጋቢት 25 ቀን 2017 ዓ.ም. በመን በረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተፈጽሟል።

**ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ በሊቀ አእላፍ ያዝ ዓለም ገሠሠ ህልፈተ ሕይወት የተሰማውን ሐዘን እየገለጸ ለወዳጅ ዘመዶ ቻቸው እና ለቤተሰቦቻቸው መጽናናትን ይመኛል**

## ስለ ሊቀ አእላፍ ያዝ ዓለም ገሠሠ የተሰጠ ቅኔ

**ጉባኤ ቃና**

ሕማም ወሞት እለዘመኑ ደቂቅ
ናሁ ረፈቁ ላዕሌሁ ለገብረ መድኅን ሊቅ

**ጉባኤ ቃና**

በግዐ ቤተ ያሬድ ያሬድ ዘመኅደሪሁ ወለጠ
እምነ ተኩላ ዓለም መሳጤ አባግዕ አምሰጠ

**መወድስ**

አዳም ወሔዋን ሰብአ ተዋርዶ
እንተ አንገሥዎ ሞት ንጉሠ ላዕሉ ወታሕውቱ
ዘኢያጸብሖ በምድር ጸባሕተ ሥጋ አልቦቱ
በሕማም ሥዩመ ዚአሁ ዘሤሞ ለዝንቱ
ወዘይቀነዮ ገብረ መድኅን
ሥጋ ጸባሕተ ጸብሐ ለውእቱ
ውእቱሂ ገብረ መድኅን ዘኢይትመዋእ በከንቱ
ሰገደ ለመንበሩ ወገረረ ለመንግሥቱ
ወኀቡረ በጽሑ ለተቀብሎቱ
ለገብረ መድኅን ጸባሔ ግብር መላእክት ሠራዊቱ
(ሊቀውንት አዕርከቱ)

**በመምህር ዘሚካኤል ገ/ኢየሱስ**
**የሊቃውንት ጉባኤ አባል**

## የቱን ትቼ የቱን ልጻፍ ?

ጀማሪ ጸሐፊ በመቅድሙ በርካታ ጉዳዮ ችን፣ ሐሳቦችን ፣ ምሥጢሮችን ፣ ለመዳሰስና ለመጻፍ ይቃጣዋል፡፡ ሁሉንም ሃሳቦች ባንድ ዓረፍተ ነገር ቢዳስሰውና ቢጨርሰውም ምኞቱ ነው፡፡ ሆኖም ግን ጽሑፍና ድርሰት ኅትመትና ንግግር በየፈረጁ፣ በየአቅጣጫው እንደሚ ጻፈው ጉዳይና እንደሚጻፍለት አን ባቢ ይለያያል፡፡ እነሆ እኔም አንዳች አጀንዳ አንስቼ ለመጻፍ ዳድቶኛል፡፡ ይሁንና የትኛ ውን ትቼ የት ኛውን ልጻፍ ትላላችሁ ?

የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ተደራ ሽነት፣ መስፋፋት ፣ መጠናከር ወይስ የልማት ጉዳይ ፣ ስለሚገነቡ ሕንጻዎች ፣ ስለ ትምህርት ቤቶችና ስለጤና ተቋማት መስፋ ፋት፣ ወይስ ስለመልካም አስተዳደር፣ ስለ ሙስና ወይም ጉቦ፣ ወይስ ስለዘረኝነትና ጎጠኝነት ፣

**የቱን ትቼ የቱን ልጻፍ ?**

የመጪው ዘመን የቤተ ክርስቲያን ፈተና ዎች ? ማለትም መዋቅሩን ለመናድ ስለ ተደ ራጁ ቡድኖች ፣ ወይስ ሊቃውንቱን በመሸጥ ስለ ሚተዳደሩት ደላሎች፣ አባቶችን ለመስ ደብ እና ለመዝለፍ ስለ ተቋቋሙ የስድብ አፎች፣ ወይስ የቤተ ክርስቲያንን አለባበስ ሥርዓት ለመዳፈር እየተንደረደሩ ስለመጡ አገልጋዮችና እና የሰንበት ተማሪዎች ጉዳይ ወይስ ፎቶአቸውንና ምስላቸውን በቤተ መቅ ደስ ብሎም በመንበሩ ይቀመጥልን ባይ የገን ዘብ ጌቶች እያቆጠቆጡ ስለ መምጣታቸው፣

**የቱን ትቼ የቱን ልጻፍ ?**

የመጪው ዘመን የቤተ ክርስቲያን ፈተና ዎች ምእመናን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመግ ባት የማኅበራት ዓባልነት መታወቂያ ግድ የሚባልበት ፣ መንፈሳዊ አገልግሎት ማግኘት በገንዘብ ብቻ የሚሆንበት ፣ ወይስ ስለ ቢዝነስ መር ማኅበራት እንቅስቃሴ ዐውደ ምሕረቶ ቻችን የሙገሳና የልመና ብቻ እየሆኑ ስለ መምጣታቸው ? ወይስ ቅዳሴ ለመቀደስ ምን ኩስናን መስፈርት እያደረጉ ስለመጡ አድባ ራት ጉዳይ፣ ዕልቅናውንም ጨምሮ ማለት ነው ስለከተማዊና ኀዳናዊ የምንኩስና ሕይ ወት መስፋፋት፣ ወይስ አሥራት በኩራት ሲጠየቁ ስለሚሳደቡ ምእመናን፣ ስለ ቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ አጀንዳዎች፣

**ታዲያስ ! የቱን ትቼ የቱን ልጻፍ ?**
**መምህር ማርቆስ ተበቃ**

# አጫጭር ዜናዎች

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርቲያን በሰሜን አሜሪካ ዩንታሃ ግዛት የማምለኪያ ሥፍራ ተረከበች

ሊቀ ትጉኃን ቀሲስ ታጋይ ታደለ የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጠቅላይ ጸሐፊ ከሦስት ዓመት በፊት ወደ ሰሜን አሜሪካ ለሥራ ባመሩበት ወቅት በአከባቢው ለሚገኘው የኋለኛው ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት፤ የተጠቀሰው ቤተ ዕምነት መሪዎች ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን መገልገያ የሚሆን ከ6 ሺ ካሬ ሜትር በላይ የሆነ መሬት ሊያበረክቱ ችለዋል፡፡



የዚህም ማምለኪያ ሥፍራ ካርታና ፕላን ጥር 5 ቀን 2017 ዓ.ም ብፁዕ አቡነ አብርሃም የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ የባሕር ዳርና ሰሜን ጎጃም አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በተገኙበት፤ የሰላም ምንስቴር ሚንስትር ዲኤታ ክቡር ከይረዲን ተዘራ ዶ/ር፣ የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ጠቅላይ ጸሐፊ ሊቀ ትጉኃን ቀሲስ ታጋይ ታደለ እንዲሁም የኋለኛው ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ተወካዮች፣ በመንበረ ፓትርያክ በመገኘት ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳ ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት አስረክበዋል፡፡

የመንግሥት አካላት በተለይም የሰላም ሚንስትር የነበሩት አቶ ብናልፍ አንዱዓለም በቦታው ርክክብ ሂደት ከፍተኛ እገዛ ማድረጋቸውን በዕለቱ የተገለጸ ሲሆን በዩነታሃ ግዛት ሰፊውን አማኝ ያላት የኋለኛው ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አመራሮች ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባበረከቱት የማምለኪያ ሥፍራ ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማቸው ለቅዱስነታቸው በሰጡት ማብራያ አስታውቀዋል፡፡

በመጨረሻም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ፣ በተደረገው ነገር መደሰታቸውን ገልጸው ይህንን ላደረጉ አካላት ምስጋና ይገባቸዋል በማለት አባታዊ ቡራኬያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

## ቅዱስ ፓትርያርኩ የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ልዑካንን በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢት ዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአኩስም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ልዑካንን በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር በትምህርተ ሃይማኖት ኅብረት ካላቸው የአኃት አብያተ ክርስቲያን መካከል የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አንዷ ስትሆን ቀደም ሲል ሁለቱ አብያተ ክርስቲያን የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በመቀራረብ ሲያከናውኗቸው የነበሩት ተግባራትና ስብሰባዎች በመላው



ዓለም ተከስቶ በነበረው የኮቪድ 19 ኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያት በተላለፉ ዓለም አቀፍ ክልከላዎች ተቋርጠው በመቆየታቸው የሁለትዮሽ ስብሰባዎቹን ለማስቀጠል እና በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለ ውን ግንኙነት ለማጠናከር ይቻል ዘንድ ከብፁዕ ወቅዱስ ባስልዮስ ማርቶማ ማቴዎስ 3ኛ የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክር ስቲያን ፓትርያርክ የተላኩት፤ ሜትሮፖሊታን ማር ዩሊዮስ እና ፋዘር ዶ/ር ጀሲ ያዕቆብን በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋግረዋል፡፡

የልዑኩ መሪ ሜትሮፖሊታን ማር ዩሊዮስ ከሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ፓትርያርክ የተላከውን መልእክትና ገጸ በረከት ለቅዱስነታቸው አቅርበው ብፁዕ



ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአኩስም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ሰላም፣ የሰው ልጆች ነጻነት፣ ፍትሕ በዓለም እንዲሰፍን በየጊዜው የሚያከናውኑትን አባ ታዊ ጥረት አድንቀው በዚህም የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተባባሪ መሆኗን ገልጸዋል፡፡

ብፁዕ ወቅዱስነታቸውም በልዑካኑ ጉብኝት መደሰታቸውን፤ እንዲሁም የአብያተ ክርስቲ ያናት አንድነት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እንዲጠናከር የሚያስፈልግበት ጊዜ መሆኑን ገልጸው በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ የሁለትዮሽ ግንኙነቱ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል፡፡

በመጨረሻም ልዑካኑ በቅዱስነታቸው ለተደረገላቸው መንፈሳዊ አቀባበል አመስግነው፤ በቀጣይም የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ቅዱሳን ፓትርያርኮች በሀገራቱ ስለሚያደርጉት ሐዋርያዊ ጉዞ ያላቸውን ተስፋ ገልጸው፤ በቅዱስነታቸው ቃለ በረከትና ጸሎት የመርሐ ግብሩ ፍጻሜ ሆኗል፡፡ በመርሐ ግብሩ ላይ ብፁዕ አቡነ አብርሃም የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ፤ የባሕር ዳር እና ሰሜን ጐጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፣ ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ የጉራጌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ እና የሚመለከታቸው የመንበረ ፓትርያርክ የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል፡፡

## ቅዱስ ፓትርያርኩ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ልዑካንን በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ልዑካንን በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት በብፁዕ አቡነ አምባ ቢመን የሚመራውን የግብፅ ኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ልዑካንን በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋግረዋል ። ልዑካኑ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ታዋድሮስ የግብጽ ኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ የተላከ የሰላምታ መልእክት ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ በማቅርብ በሁለቱ ተቋማት መካከል የነበረውን የጋራ ትብብር በማጠነከር ላይ ውይይት አድርጓል። እንደ ልዑካኑ ገለጻ ከዚህ



በፊት በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገር የሚገኙ የጋራ የመገልገያ ሥፍራዎችን በጋራ መጠ ቀም የሚያስችል አንድነት የነበረን በመሆኑ አሁ ንም የተለመደውን ሥራ ማለትም የኢት ዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ በምትገኝበት ቦታ ሁሉ የኮፕቲክ ቤተክርስቲያን እንድትገለገል የኮፕትክ ቤተክርስቲያን ባለችበት ሁሉ የኢት ዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መገልገል እንድትችል የሚያስችል ሁኔታን ማስቀጠል ነው ብለዋል ።

ልዑካኑን በጽሕፈት ቤታቸው ያነጋገሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ይዘውት የመጡት ሐሳብ የነበረና በመገልገያ ሥፍራ በማጣት የሚቸገሩ ምእመናን የሚታደግ ሐሳብ ነውና በአድ ናቆትና በደስታ ተቀብለነው እየተገበርነው ያለ ቢሆንም አሁንም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ታዋድ ሮስም ይህንን የሰላም መልእክተኛ እና በሁለ ቱም ተቋማት ውስጥ የሚገለገሉ ምእመናን ችግርን የፈታ ሐሳብ በልዑካኑ በኩል የማጠ ናከሪያ ሐሳብ እንድንሰጥበት ስላደረጉ እናመ ሰግናለን ብለዋል።

በመቀጠልም ልዑካኑ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ታዋድሮስ የግብፅ ኮፕቲክ ፓትርያርክ የተላከውን ስጦታ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእ ጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ያስረከቡ ሲሆን ቅዱስነታቸውም ስለ ስጦታው አመስ



ገነዋል። በመጨረሻም ልዑካኑ ስለተደረ ገላቸው መልካም አቀባበልና ይሁንታ መደሰ ታቸውን ገልጸው የቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በኢትዮጵያውያን ምእመናን ትከሻ ተሠርቶ ማለቁ እጅግ ደስ እንዳሰኛቸው በመግለጽ የግብጽ ኮፕቲክ እንደ ተለመደው በካቴድራሉ መገልገል የሚችሉበት መንገድ ስለ ተመቻቸ ላቸው አመስገነው የውይይቱ ፍጻሜ ሆኗል።

# ቅዱስ ፓትርያርኩ የአክትስ ቸርች ኦፍ ሱዊዲን የሥራ ኃላፊዎችን በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት የአክትስ ቸርች አፍ ሱዊዲን የሥራ ኃላፊዎችን በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ።

ለበርካታ ዓመታት ከክርስቲያናዊ ተራድኦና ልማት ኮምሽን ጋር በመተባበር የአስቸኳይ የምግብና ምግብ ያልሆኑ ርዳታ በማቅረብ፣ የመልሶ ማቋቋም ሥራ ላይ ዘርፈ ብዙ ቁሳቁሶችን በማገዝ ፣ ለአርሶ አደሮች የምርጥ ዘር በማቅረብ፣ በፕሮጀክት የታቀፉ የአርሶ አደሩን ምርታማነት የሚጨምሩ ሥራዎችን በማገዝ፣አቅመ ደካማ እናቶችን በከብት ርባታ ራሳቸውን እንዲደግፉ በመርዳት፣ በጤና ፣ በሕፃናት ምገባ እና በአቢያተ ክርስቲያናት አጸድ ልማት ዙሪያ በመሥራት እንዲሁም ዘርፈ ብዙ ክንውኖችን ሲያከናውን የነበረው የሲውዲን ቤተክርስቲያን የልማት ክንፍ ኀላፊዎች ከጥር 29 ቀን 2017 ዓ.ም እስከ የካቲት 1 ቀን 2017 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ቆይታ ለማድረግ የመጡ ሲሆን በቆይታቸው ማገባደጃ ላይ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩን ለማግኘት በልማት ኮምሽን የበላይ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ ሳሙኤል አማካኝነት ፕሮግራም እንዲያዝላቸው ተደርጎ ከቅዱስነታቸው ጋር ውይይት አድርገዋል።



***በውይይቱ***

- ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል የክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮምሽን፣ የቤቶችና ሕንጻዎች አስተዳደር ድርጅት ሊቀ ጳጳስ
- ኤሪክ ሌይሰን የአክትስ ቸርች ኦፍ ሲውዲን የግሎባል ዳይሬክተር
- ካሪክ ሁግሰን የአክትስ ቸርች ኦፍ ሲውዲን የፖሊሲ አማካሪ
- አቶ ብርሃኑ ይስማው የአክትስ ቸርች ኦፍ ሲውዲን በኢትዮጵያ ተወካይ
- ኢንጂነር ይልቃል ሽፈራው የልማት ኮምሽን ኮምሽነር መልአከ ሕይወት ቆሞስ አባ ኃይለ ገብርኤል ነጋሽ የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ልዩ ጽሕፈት ቤት ዋና ጸሐፊ እና ሌሎችም በኮምሽኑና በብፁዕ ወቅድስ ፓትርያርክ ልዩ ጽሕፈት ቤት የሚገኙ ሠራተኞች ተገኝተዋል።

በውይይቱ ድርጅቱ ለዓመታት በሰበአዊ ርዳታ፣ በቤተክርስቲያን አጸድ ጥበቃ፣ በልማት እና በኢኮኖሚ፣ በጤና እና በሕፃናት ምገባ ላይ ያደርገው የነበረውን እገዛ እውቀና የሰጠና ከዚህ በኋላም በልዩ ልዩ ሥፍራ አስፈላጊ የሆኑ ሥራዎችን ለማገዝ የሚያስቸል ነው ።

መርሐ ግብሩን የመሩት የኮምሽኑ ኮምሽነር ኢንጂነር ይልቃል ሽፈራው ሁሌ እንደምና ደርገው በደብዳቤና በሪፖርት ከመገናኘት ባሻገር እንዲህ ገጽ በገጽ ተገናኝተን መነጋገሩ ለሥራችን ሠፊ መንገድ ይከፍታል ብለን እነዚህ ከፍተኛ የሥራ ኀላፊዎችን ይዘን መጥተናል። ከድርጅቱ ጋር የነበረን የሥራ ግንኙነት ከቅዱስነትዎ የተሰወረ ስላልሆነ እነዚህን የሥራ ኃላፊዎች እንዲባርኩልን በማለት ቅዱስነታቸውን ጋብዘዋል።

ቅዱስነታቸውም ንግግራቸውን ሲጀምሩ የሚፈናቀል፣ የሚሰደድ፣ የሚራብና የሚጠማ እንዲሁም በመድኃኒት እጦት የሚሰቃይ ሰው ባለበት ዘመን እጁን ለእርዳታ የሚዘረጋ ሰው መኖሩ የእግዚአብሔር ቸርነቱ እንዳልተለየን ትልቅ ማሳያ ነው። በርግጥም እናንተ የቸርነት ሰዎች ወደ ሀገራችን በመምጣት በልዩ ልዩ ዘርፍ ስለምትረዱን እናመሰግናለን። ያኔ በሰላም በምንኖርበት ዘመን ከጎናችን እንደነበራችሁ ሁሉ አሁንም ግማሹ በጦርነት፣ ሌላው በኑሮ ውድነት እየተሰደደ ባለበት ዘመን ከጎናችን በመሆናችሁ የዘመናት ታማኝ አጋሮቻችን መሆናችሁን ተገንዝበናል። በመሆኑም ስለምታደርጉልን ማንኛውም ትብር ሁሉ በጣም እናመሰግናለን። የሰው ልጅ ሰውነቱ የሚለካው ለወንድሙ በሚያደርገው እገዛ ነው። ዓለማችን ካልተረዳዳች ልትቀጥል አትችልም። ይህ ገብቷችሁ መረዳዳትን ሥራችሁ አድርጋችሁ ከእኛም ጋር ስለምትሠሩ በጣም እናመሰግናለን ብለዋል።

የቅዱስነታቸውን የምስጋና ቃል የሰሙት ሚስተር ኤሪክ ስለተደረገልን አቀባበል እናመሰግናለን ከዚህ በፊት እናደርገው እንደነበረው እርሱን እንቀጥላለን። ይህ ዘመን ክርስቲያኖች አንድነት ፈጥረው እንዲንቀሳቀሱ ያስገደደ ዘመን ነውና እኛም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር ተባብረንና አንድነት ፈጥረን እየሠራን በመሆኑ ደስታችን ወደር የለውም ብለዋል።

በመጨረሻም ይህንን ሥራ በሲውዲን እያንቀሳቀሱ ላሉ ኀላፊዎች በክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮምሽን የተዘጋጀ ስጦታ በቅዱስነታቸው ተበርክቶ የውይይቱ ፍጻሜ ሆኗል።

# ቅዱስ ፓትርያርኩ በእሥራኤል ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የተመራ ልዑክን በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአኩስም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በእስራኤል ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የተመራ ልዑክን በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ፡፡

ብፁዕ ወቅዱስነታቸው በዛሬው ዕለት የእሥራኤል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር የሆኑትን ክብርት ሻረን ሃስኬል፣ በኢትዮጵያ የእሥራኤል አምባሳደር ክቡር አብርሃም ንጉሤን እና ከፍተኛ የሥራ ሓላፊዎችን በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋግረዋል፡፡



ክብርት ምክትል ሚኒስቴር ሻረን ሃስኬል በጽርሐ መንበረ ፓትርያርክ ለእርሳቸውና ለመጡት ልዑካን በተደረገላቸው የክብር አቀባበል መደሰታቸውን ገልጸው እሥራኤል የምትገኝበትን ወቅታዊ ሁኔታ፤ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያለውን ግንኙነት አጠናክሮ ለማስቀጠል በእሥራኤል ሀገር መንግሥት በኩል ያለውን ፍላጎት አስረድተዋል፡፡

ቅዱስነታቸውም የሃይማኖት መሠረት የሆነችው እሥራኤል ከኢትዮጵያ ጋር ያላት ግንኙነት ከዘመነ ኦሪት ጀምሮ ሰፊ ትስስር ያለው መሆኑን በማስታወስ ዓለም በልዩ ልዩ መልኩ እየተፈተነች ባለበት ወቅት በእሥራኤልና ፍልስጥኤም መካከል ተከስቶ በቆየው ጦርነት የተሰማቸውን ጥልቅ ሐዘን ገልጸው በኢየሩሳሌምና አካባቢዋ የሚገኙ ገዳማት፣ አብያተ ክርስቲያናት፣ አብያተ እምነት እና ታሪካዊ ቦታዎች በጦርነቱ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ጥበቃ በማድረግ የእሥራኤል መንግሥት የወሰደውን ጥንቃቄ በማድነቅ አመስግነዋል፡፡

ቅዱስነታቸው ከእሥራኤል ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር ባደረጉት ሰፊ ውይይት ቤተ ክርስቲያናችን ከእሥራኤል መንግሥት ጋር በጋራ የምታከናውናቸው ተግባራትን የቤተ ክርስቲያኒቱን ሕግጋት ባከበረ መልኩ ማዕከላዊ አሠራርን በመጠበቅ አጠናክሮ ማስቀጠል በሚቻልበት ዙሪያ ከመግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

# ቅዱስ ፓትርያርኩ አዲሱን የጀርመን ምክትል አምባሳደር በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት አዲሱን የጀርመን ምክትል አምባሳደር በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ፡፡

መጋቢት 11 ቀን 2017 ዓ.ም በኢትዮጵያ የጀርመን ምክትል አምባሳደር የሆኑት ዶክተር ፈርድናንድ ቮን ዌይሂ በኢትዮጵያ በአዲስ አበባ የተመደቡበትን የሥራ ኃላፊነት ለመጀመር ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ሲሆን፤ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ጋር ትውውቅ አድርገዋል፡፡



ምክትል አምባሳደሩ እንደተናገሩት “ለእኔ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የበለጠ መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም በዚህች ሀገር ውስጥ ስለ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ማወቅ ለብዙ ሰዎች በጣም ጠቃሚ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ስለዚህ እኔም በተያዘልኝ ቀጠሮ መሠረት ከጀርመን ኤምባሲ በመምጣት ከቅዱስ ፓትርያርኩም ቡራኬ ተቀብዬ ስለ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ለማወቅ ችያለሁ” ብለዋል፡፡

ምክትል አምባሳደሩ አያይዘውም “በአሁኑ ወቅት የዐቢይ ጾም ወቅት በመሆኑ፤ ኦርቶዶክሳውያን በጾም፣ በጸሎት በየአብያተ ክርስቲያንቱ ነው ያሉት፡፡ ይህ ሥነ ሥርዐት በጀርመን ሀገር ከምናየው የተለየና አስደናቂ ነው፡፡ በተዘዋወርኩባቸው ቦታዎች ሁሉ በተለይም አብያተ ክርስቲያናት በሚገኙባቸው ቦታዎች በየዕለቱ ሰው በቤተክርስቲያን ይገኛል፣ የሚሰማው የቅዳሴ ድምፅ የተለየ ነው፡፡ ይህ በጣም አስደናቂ ተሞክሮ ነው።” ብለዋል፡፡

ምክትል አምባሳደሩ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጋር በትብብር ስለሚሠሩት ሥራም አብራርተዋል “የልምድ ልውውጥ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ አንድ መጥቀስ የምፈልገው ነገር ቢኖር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ልማት ኮሚሽን ጋር ስለ ደን ጥበቃ በትብብር የምንሠራው ሥራ አለ፡፡ በኢትዮጵያ ክልል በአየር ስትበሩ አንዳንድ አረንጓዴ ጥቅጥቅ ያሉ የደን ደሴቶችን ታያለህ። በዚህ ደሴት መካከል ቤተክርስቲያን አለች፡፡ ቤተክርስቲያን ደኖችን ጠብቃ ያቆየቻቸው ናቸው፡፡ ሰዎችም ቤተ ክርስቲያኗ የምታስተምረውንም ስለሚሰሙ ዛፎችን አይቆርጡም፡፡ ስለዚህ ስለ ደን ጥበቃ የቤተክርስቲያኗ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ እኔ እንደማስበው እነዚህን አረንጓዴ ደሴቶች በመሬት ገጽታ ላይማስቀመጥ እና የበለጠ ማማስፋት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እናም ይህንን አረንጓዴነት በመደገፍ አብረን እንሠራለን” ብለዋል፡፡

በመጨረሻም ምክትል አምባሳደር ዶክተር ፈርድናድ ቅዱስነታቸው በጽሕፈት ቤታቸው ተቀብለው ስላነጋገሯቸው፣ በተደረገላቸው አቀባበልና ቅዱስነታቸው ስለሰጧቸው ቡራኬ አመስግነዋል።

# ቅዱስ ፓትርያርኩ ከማኅበረ ቅዱሳን አመራሮች ጋር ተወያዩ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ከማኅበሩ አዲሱ ሥራ አመራር ጉባኤ አባላት ጋር መጋቢት 9 ቀን 2017 ዓ.ም ውይይት አደርገዋል።

በውይይቱ ማኅበረ ቅዱሳን እያከናወነ ያለውን አገልግሎትና የተገኙ ውጤቶችን አብራርቷል። ቅዱስነታቸውም ማኅበሩ አገልግሎቱን አጠናክሮ እንዲቀጥል በተለይ ለሀገራችን ሰላም እንዲመጣ እና በተለያዩ ምክንያቶች የተፈናቀሉና የተራቡ ወገኖቹን በመርዳት ላይ የበለጠ እንዲሠራ መመሪያ ሰጥተዋል፡፡

በመጨረሻም ቅዱስነታቸው ለማኅበሩ ሥራ አመራር ጉባኤ አባላት አገልግሎታቸው የሰመረ እንዲሆን ቡራኬ ሰጥተዋቸዋል፡፡

# የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አንድነት ለመንፈሳዊ ትምህርት መስፋፋት በሚል ርእስ ጉባኤ ተካሄደ

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አንድነት ለመንፈሳዊ ትምህርት መስፋፋት በሚል ርእስ የሁለት ቀናት የውይይትና የምክክር ጉባኤ ቅዱስ ፓትርያኩ በተገኙበት በጽርሐ ተዋሕዶ አዳራሽ መጋቢት 25 እና 26 ዓ.ም ተካሄደ፡፡

በጠቅላይ ቤተ ክህነት ትምህርትና ማሰልጠኛ መምሪያ አዘጋጅነት በተካሄደው ጉባኤ ላይ የዘጠኙ የቤተ ክርስቲያኒቱ ከፍተኛ መንፋሳዊ የትምህርት ተቋማት የሥራ አመራሮች የተገኙ ሲሆን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የትምህርት ተቋማቱ




ቤተ ክርስቲያኒቱን በታማኝነት የሚያገለግሉ እንዲሁም ሓላፊነትን የሚሸከሙ ደቀ መዘሙ ርትን ማብቃት እንደሚጠበቅባቸው አጽንኦት በመስጠት መልእክት አስተላልፈዋል፡፡

ብፁዕ አቡነ አብርሃም የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ የባሕር ዳርና ሰሜን ጎጃም አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በበኩላቸው ጥራት ያለው ደቀ መዛሙርትን ላማፍራት ወጥ የሆነ የትምህርት ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ በጉባኤው መክፈቻ ላይ የመምሪያው ዋና ሓላፊ መጋቤ ሐዲስ ኃ/እግዚእ አሰፋ የጉባኤው መዘጋጀት በተመለከተ ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን የመምሪያው ዋና ጸሐፊ መጋቤ ብሉይ አእመረ አሸብር ሃይማኖትና ትምህርት ምን ያገናኛቸዋል በሚል ርእስ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

የየተቋማቱ የሥራ ሓላዎች የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ያቀረቡ ሲሆን በየጊዜው እየጨመረ የመጣው የቁሳቁስና የእህል ዋጋ መናር የበጀት ዕጥረት በማስከተሉ  በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ እንቅፋት እየፈጠረባቸው ስለመሆኑ ጠቁመው ቅዱስ ሲኖዶስ ትኩረት እንዲሰጥ አሳስበዋል፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስር አንድ መንፈሳዊ ዩኒቨርስቲ እና ስምንት መንፈሳዊ ኮሌጆች ይገኛሉ፡፡

# ‹‹እምቅድመ ዓለም›› በሚል ርእስ የተዘጋጀ መንፈሳዊ መዝሙር ተመረቀ



በዘማሪት ጋዜጠኛ ሰላም አምባዬ በአማርኛና በት ግርኛ ቋንቋዎች የተዘጋጀ ቁጥር 2 ዝማሬ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት መጋቢት 28 ቀን 2017 ዓ.ም ተመርቆ ለአደማጭ ተለቋል፡፡

ዘማሪት ጋዜጠኛ ሰላም አምባዬ ከዚህ ቀደም በትግርኛ በግል በአማርኛ በሕብረት መዝሙሮችን ለአድማጭ ጆሮ ማድረሷ የሚ ታወቅ ሲሆን መዝሙራቱም መሶበ ወርቅ በተሰኘ የዩቲዩብ መስመር እንደሚገኙ ተገልጿል፡፡

# የመጽሐፍ ዳሰሳ

*የመጽሐፍ ዳሰሳ*
*የመጽሐፉ ርዕስ፡- ግብረ ሕማማት*
*የገጽ ብዛት፡-1196*
*የታተመበት ዓ.ም፡-1990 ዓ.ም/ ሁለተኛ እትም*
*አሳታሚ፡- ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት*
*የታተመበት ቋንቋ፡- ግእዝ እና አማርኛ*


ግብረ ፡ ሕማማት ።
ይህ ፡ መጽሐፈ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡
በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ
አዲስ ፡ አበባ ፡

ግብረ ሕማማት በሰሙነ ሕማማት ብቻ የሚነበብ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሕማምና መከራ ፣የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም መሪር ኃዘን የሚያወሳና የሚዘክር ከአዋልድ መጻሕፍት አንዱና ዋነኛው ተብሎ የሚጠቀስ መጽሓፍ ነው፡፡

መጽሐፉ አዋልድ ይባል እንጂ መላ ይዘቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ባላነሰ ብሉያትንና የሐዲሳትን የሚተነትን የቤተ ክርስቲያናችን ድንቅ መጽሐፍ ነው፡፡

መነሻውም፡- ሐዋርያት በኢየሩሳሌም ካሉ ምእመናን ጋር መጾም እና ትንሣኤውን ማክበር ሲጀምሩ በጽርሐ ጽዮን ተብስበው በደነገጉት የቤተ-ክርስቲያን ሥርዓት “እናንተ ግን ጠብቃችሁ መከራ መስቀሉን መታሰቢያ ሕማማቱን አክብሩ”ሲሉ አዘዋል።

ሆኖም ግን እንደዛሬው ጊዜውን አልወሰኑትም ነበርና በሊቀ ጳጳስ ድሜጥሮስ ቀመር ከዐቢይ ጾም ቀጥሎ እንዲሆን ተወስኗል።

ተያይዞም ሕማሙን የሚያትተው ይኸው ግብረ ሕማማት የተሰኘው መጽሐፍ በ14 ኛው ምእት ዓመት ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ዋለ።

ከዚያም ከ1340-1380 የነበሩት ብፁዕ አቡነ ሰላማ ብርሃነ ዐዜብ ከአረብኛ ወደ ግእዝ እንደተረጎሙት ተጽፏል።

ግብረ ሕማማት ለብዙ ዘመናት በግእዝ ብቻ የሚገኝ መጽሐፍ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው ሕዝበ ክርስቲያን እንዲሰማው እና ግእዝን የማያውቅ ሰው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚነገረውን መከራ በደንብ እንዲገባው በሚል በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ዘመነ ፐትርክና ሊቀ መዘምራን ላዕከ ማርያም ወ/ኢየሱስ በተባሉ ሊቅ ወደ አማርኛ ተተርጉሟል፡፡

በግእዝ የነበረው መጽሐፍ በዕለታት እና በሰዓታት ብቻ የተከፈለ እንጂ ምዕራፍ ክፍል እና ቁጥር አልነበረውም።

ይህ የአማርኛው መጽሐፍ ግን በምዕራፍ እና ክፍሎች የተከፋፈለ ሲሆን ለአጠቃቀምም ምቹ ነው።

ግብረ ሕማማት በውስጡ የነገረ ሃይማኖት፣ የታሪክ፣ የተአምራት፣ የሥርዓትና የሕግ መጽሐፍትን ይዟል። ለምሳሌ ወቅቱን የሚመለከቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን፣ ኦሪትን፣ ነቢያትን፣ ሐዲሳትን፣ ሃይማኖተ አበውን፣ ተግሳጽን፣ ተአምረ ኢየሱስን ተአምረ ማርያምን፣ ወዘተ የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡

ለመጽሐፈ ግብረ ሕማማት ይዘት እንቁ የሆኑት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ቅዱስ ያሬድና አባ ጊዮርጊስም የጸሎትና የዜማ አስተዋጽኦዋቸውን በማካተት አሻራቸውን አሳርፈውበታል፡፡

የመጽሐፉ ምዕራፍ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን በመጀመሪያው ክፍል ሰዓት ከኦሪት እና ከነቢያት የተውጣጡ ምንባባት ይገኛሉ።

በሁለተኛው ክፍል ከሊቃውንት፣ ከድርሳናት፣ ከተግሳጽ እና ከተአምራት የተውጣጡ ምንባባት ይገኛሉ።

በሦስተኛው ምዕራፍ ቅድመ ወንጌል፣ ድኅረ ወንጌል፣ በእንተ ጽንዐ ዛቲ እና እስከ ማኅተመ ጸሎት(የየሰዓቱ የጸሎት ፍጻሜ) ይነበባሉ።

በተጨማሪም ምዕራፉ የጸሎትና የስግደት ሥርዓት የሚፈጸምባቸው ጊዜያትን የሚከፍል ነው፡፡

ግብረ ሕማማት ሲነበብ ከቻልን በአፀደ ቤተ-ክርስቲያን ተገኝተን ካልሆነም በያለንበት ስፍራ ሆነን የጌታችንን ሕማሙን፣ እጅግ ልብ የሚሰብር የእመቤታችንን ኃዘኗን ማሰብ ይገባናል። እንበለ ደዌ ወሕማም እንበለ ጻማ ወድ ካም አመ ከመ ዮም ያብጽሐነ ያብጽሕከሙ እግዚአብሔር እስከ ትንሣኤሁ በፍሥሐ ወበ ሰላም አሜን !

# ስብከተ ወንጌል በዘመናት

“ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ የተከደ ነባቸው ለሚጠፉ ነው። ለእነርሱም የእግዚ አብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ”. አሳ(፩.ቆሮ. ፬:፫-፬)።

*መግቢያ*

የቤተ ክርስቲያን ብርሃንዋ ወንጌል ነው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በወንጌል ብርሃንነት የዓለም ጨለማን የምታበራ ፥ የአለማወቅ ድንቁርናን እያበራች ወደ ብርሃን ክርስቶስ መንጋውን የምትሰበስብ የማትጠፋ ማኅቶተ ብርሃን ናት። ጨለማ ብርሃንን እንደማ ያሸንፍ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን የሚያሸንፍ ምድራዊ ኃይል የለም። በየዘመናቱ ብዙዎች አጽራረ ቤተ ክርስቲያን ቢነሱም ጊዜያቸውን ተጠቅመው ከጊዜያቸው ጋር አልፈዋል። ቤተ ክርስቲያን ግን አለች። ትቀጥላለችም። ዘመ ናትን አሳልፋ ፥ ጠላቶችዋንም ሸኝታ እርስዋ በየትኛው ኃይል ባለመገታት በድል ጎዳና እያበበች የምተገሰግሰው በውስጥዋ የማይ ሸነፍ ኃይል እርሱም መሥራችዋ ክርስቶስ ስለሚጠብቃት ነው።

ክርስቶስንና ቤተ ክርስቲያንን በፍጹም ፍቅር የሚያስተሣስርም “የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን” የተባለው ነው። ቤተ ክርስ ቲያን በደሙ ተዋጅታ ክብሩን ተጎናጽፋ ለዓለም የተገለጠችው በወንጌል ብርሃን ነውና። የሰው ዘር ሁሉ ዓይኑ ተገልጦ ፥ ልቦ ናው በርቶ ቤተ ክርስቲያንን የሚያያትና የሚጠለልባት በወንጌል ብርሃን ነው። የቤተ ክርስቲያን መሠረትዋ ፥ ህልውናዋ ፥ ክብርዋ እና ተስፋዋ ወንጌል እንደ ሆነ ቅዱሳት መጻሕ ፍት የሚመሠክሩት ሐቅ ነው። ይህም ስለሆነ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለስብከተ ወንጌል ትተጋለች። እስትንፋስዋ ነውና ስብከተ ወን ጌልን እንደ ዓይን ብሌን ትመለከ ታለች።

### ሀ. ስብከተ ወንጌል ለቤተ ክርስቲያን

1. **ቀዳሚ ተልእኮዋ**

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱሳን ሐዋርያትን የጠራቸው ለምን ዋና ዓላማ እንደ ሆነ ሲገልጽ “ኢየሱስም፡- በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋች ኋለሁ አላቸው” (<u>ማርቆስ ፩፥፲፯</u>) ይላል። የቅዱሳን ሐዋርያት ጥሪና ተልእኮ የቤተ ክርስ ቲያን ጥሪና ተልእኮ በመሆኑ ቅዱሳን ሐዋር ያት በክርስቶስ የተመሠረቱ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ናቸውና። በትምህርተ ክር ስትና ቅደም ተከተል ስንቃኘው ስብከተ ወን ጌል የመጀመሪያና የክርስቶስ የመገለጥ መሠረ ትም ነው። ቅዱስ መጽሐፍ የወልደ እግዚአ ብሔር ፥ የወልደ ማርያም የኢየሱስ ክርስቶስን የአገልግሎት ጅማሬ ሲናገር “እየሰበከ... መጣ” “ይሰብክ ነበር” (ማር.1፥15 ፤ ማቴ.4፥17) ይላል እንጂ እየዘመረ ፥ እየቀደሰ ፥ እያስተ ዳደረ መጣ አይልም። እነዚህ የሥራ ዘር ፎች ሁሉ ለስብከተ ወንጌሉ ድጋፍ የሚሰጡ ፥ ስብከተ ወንጌልን ለማሳለጥ የተፈጠሩ የአገል ግሎት ዓይነቶች ናቸው። አንድ ሰው በመጀ መሪያ የምሥራቹን ቃል “ስብከተ ወንጌልን” ሰምቶ ያምናል። ከአመነ በኋላ ተጠምቆ ምሥ ጢራተ ቤተ ክርስቲያን ይፈጸሙለታል። (በቅብዐ ሜሮን ታትሞ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ይቀበላል።) የቤተ ክርስቲያን አባል ሆኖ ምእመን፥ ክርስቲያን ፥ የክርስቶስ አካል ተብሎ ይጠራል። ከዚያ በኋላ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን መደበኛ ትምህርት ይማ ራል። ስለዚህ ከመደበኛ ትምህርትም እንኳ ስብከተ ወንጌል ይቀድማል ማለት ነው።

ስለሆነም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን “ስብከተ ወንጌል” የመጀመሪያ ተልእኮዋ መሆኑን በህጎች ፥ በደምቦች ፥ በመመሪያዎች አሥፍራ እንዳስቀመጠችው ሁሉ በአግባቡ ሊፈጸም ይገባል። የቤተ ክርስቲያን መዋቅር በየደረጃው ቀዳሚና የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ የሆነውን ስብከተ ወንጌል ትኩረት በመስጠት ፍልሠተ ምእመናንን ልገታ ይገባል።

**2. የመኖር ህልውናዋ**

ቤተ ክርስቲያን ህልውናዋ በክርስቶስ ሰው መሆን ላይ የተመሠረተ ነው። የተመ ሠረተችበትም ዓለት ሕያው ዓለት ሲሆን ይህም ዓለት ቅዱስ ጴጥሮስ ወልድ ዋህድ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አምኖ የመሠከረው እውነት ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ ይህን እውነት በመመሥከሩ ምሥክርነቱ ዓለት እንደ ሆነ ፥ የመሠከረውም ምሥክርነት ከራሱ ሳይሆን ከላይ ከእግዚ አብሔር የተሰጠው መሆኑንና በዚህም ብፁዕ መባሉን የእግዚአብሔር ቃል ያስረዳናል። “ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው። የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ። እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉ አትም” (ማቴ.፲፮:፲፯-፲፰)።

ይህም ህልውናዋ በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንን ተመርኩዞ በመለ ኮታዊ አሠራር ላይ የተመሠረተ በየትኛውም ሥጋዊና አጋንንታዊ ኃይል የማይቻል መሆኑን ሲያረጋግጥልን “የገሃነም ደጆችም አይችሉ አትም” ብሏል። በመሆኑም ቤተ ክርስቲያን የምትመሠረተው በስብከተ ወንጌል ሲሆን የኖረችውና የምትኖረውም በኢየሱስ ክርስ ቶስ የደሙ ኃይል ተገንብታ በወንጌል እያበ በችና የጨለማውን ኃይል እየገረሰሰች ነው።

**3. የጽድቅ ፍሬን የማፍራት ዋስትናዋ**

ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ራስነት ያለች አካሉ ፥ በክርስቶስ የወይን ግንድነት ላይ የበቀለች የወይኑ ቅርንጫፍ ስለሆነች ዋስት ናዋ በክርስቶስና ከክርስቶስ ጋር ተጣብቃ የመኖር ሕይወት ነው። የክርስቲያኖችን አን ድነት የምትወክል ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የህልውና ወስትናዋ የክርስቶስ በእርሷ የመ ኖርና እርሷ ከእርሱ ጋር የመኖር ብቻ እንደ ሆነ እርሱ ራሱ እንዲህ ይላል: “እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል። በእኔ የማይኖር ቢሆን እንደ ቅርን ጫፍ ወደ ውጭ ይጣላል ይደርቅማል፤ እነር ሱንም ሰብስበው ወደ እሳት ይጥሉአቸዋል፥ ያቃጥሉአቸውማል” (ዮሐ.፲፭:፭-፮)።

**በቀጣይ ኅትመት ይጠብቁ**

**በመ/ሰ ቆሞስ አባ ቃለ ጽድቅ ሙልጌታ (ዶ/ር)**

# ዐሥራ ሦስቱ ሕማማተ መስቀል



በሰሙነ ሕማማት ጠቅለል ባለ መልኩ የምናስባቸው የጌታ ችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሕማ ማት ዐሥራ ሦስት ናቸው፡፡ እነርሱም ዐሥራ ሦስቱ ሕማ ማተ መስቀል ይባላሉ፡፡

1. ተኰርዖተ ርእስ (ራስን በዘንግ መመታት)

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክር ስቶስ ራሱን በዘንግ መመታ ቱንና መቀጥቀጡን የሚገልጥ ነው፡፡ ‹‹ተኰርዖት›› የሚለው ቃል ኩርዐ - መታ ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ነው፡፡

ርእስ ደግሞ ራስ ማለት ነው፡፡ አገረ ገዥው ጲላጦስ ‹‹እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ›› ብሎ እጁን ከታ ጠበ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ገርፎ ለካህናት አለቆ ችና ለሸማግሎች አሳልፎ ሰጥቶት ነበር፡፡ በአይሁድ ሕግ የተገረፈ አይሰቀልም፤ የሚሰ ቀል ደግሞ አይገረፍም፡፡ እርሱ ጲላጦስ ግን ከገረፈው በኋላ፣ የበደል በደል፣ እንዲ ሰቅሉት አሳልፎ ሰጣቸው፡፡ [ማቴ 27:24፤ ማር 15:15፤ ሉቃ 23:25፤ ዮሐ 18:39]፡፡

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተላልፎ ከተሰጠ በኋላ የእሾህ አክሊል ጐንጉነው ራሱ ላይ ደፍተውበታል፡፡ ራሱንም በዘንግ መትተውታል [ማር 1:19]፡፡ የሰው ዘር ከአዳም ጀምሮ በጠላቱ በዲያብሎስ በተጐነጐነ የኃ ጢአት እሾህ ራሱ ተይዞ ነበርና ይህንኑ ለማስ ወገድ ከሰማይ የወረደ ሰማያዊ የሆነ ዳግማዊ አዳም ክርስቶስ በጠላቶቹ በአይሁድ ተንኮል የተጐነጐነ አክሊለ ሦክ እንደዘውድ ደፉ፡፡

በሲኦል ወድቆ በዲያብሎስ ተረግጦ ራሱ የሚቀጠቀጠውን የሰውን ልጅ ለማዳን መድኃ ኔዓለም ክርስቶስ ራሱን በመቃ ተቀጠቀጠ፡፡ ከራሱ ላይ በሚወርደው ደም ፊቱ ተሸፈነ፡፡

2. ተፀፍዖ መልታሕት (በጥፊ መመታት)

አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እጃቸው በደም፣ ጣቶቻቸው በበደል በረከሰ በአይሁድ እጅ በጥፊ መመታቱን የሚገልጥ ነው፡፡ ‹‹ተፀ ፍዖ›› የሚለው ቃል ፀፍዐ በጥፊ መታ ከሚ ለው የግእዝ ግሥ የወጣ ነው፡፡ መልታሕት ደግሞ ፊት፣ ጉንጭ ማለት ነው፡፡

ጌታችን ለሊቀ ካህናት ቀያፋ እውነትን መናገር እንደ ስድብ ተቆጥሮበት መላልሰው ፊቱን በጥፊ መትተውታል፡፡ ፊቱንም በጨ ርቅ ሸፍነው ‹‹ክርስቶስ ሆይ በጥፊ የመታህ ማነው? ትንቢት ተናገርልን›› እያሉ ዘብተው በታል፡፡ በጠላት ዲያብሎስ እጅ ወድቆ በነፍሱ ይቀለድበትና ይንገላታ የነበረውን የሰውን ልጅ ለማዳን ብሎ በጠላቶቹ በአይ ሁድ እጅ ወድቆ ተጐሰመ፤ ተንገላታ፤ በጥ ፊም ተመታ [ማቴ 27:27]፡፡ ጲላጦስ አሳልፎ ከሰጠው በኋላም አክሊለሦክ በራሱ ላይ አኑረው ቀይ ልብስ አልብሰው ‹‹የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፣ ሰላም ለአንተ ይሁን›› እያሉ እየተሳለቁበት በጥፊ መትተውታል [ዮሐ 19:2-4]፡፡ “አላወቁትም እንጂ እርሱ በመን ግሥቱ ሽረት፣ በባሕርዩ ሞት የሌለበት የዘለ ዓለም አምላክ ነው፡፡

3. ወሪቀ ምራቅ (ምራቅ መተፋት)

ርኩሳን አይሁድ በብርሃናዊው የክርስቶስ ፊት ላይ በሚያስጸይፍ ኹኔታ ምራቃቸውን እንደተፉበት የሚገልጥ ነው፡፡ ‹‹ወሪቅ›› የሚ ለው ቃል ወረቀ ካለው ግእዛዊ ግሥ የተገኘ ነው፡፡ ትርጉሙም እንትፍ አለ፣ (ተፋ) ማለት ነው፡፡ በነቢዩ በኢሳይያስ መጽሐፍ [ምዕራፍ 50:6] ‹‹ፊቴንም ከውርደትና ከትፋት አልመለስኩም›› ተብሎ እንደተነገረ እየዘበቱበት ምራቃቸውን ተፉበት [ማቴ 27:29-30፤ ማር 15:19]፡፡ በኃጢአት የቆሸ ሸውን የሰውን ሕይወት ለማጥራት የመጣው ንጹሐ ባሕርይ አምላክ ተተፋበት፡፡ በሥራው ከገነት ተተፍቶ፤ ተንቆ፤ ተዋርዶ የነበረውን የሰውን ልጅ ለማዳን ኃጢአትን ይቅር የሚል እርሱ ጌታችን ያለ ኃጢአቱ ተተፋበት፤ ተናቀ፤ ተዋረደ፡፡ እንኳን በአምላክ ፊት በሰው ፊት እንኳን መትፋት እጅግ ያስነውራል፡፡ እርሱ ግን የኃጢአታችንን ነውር ከእኛ ሊያጠፋ ነውር የሆነውን ምራቅ ተቀበለ፡፡

4. ሰትየ ሐሞት (መራራ ሐሞት መጠጣት)

ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመልዕልተ መስቀል ሳለ ተጠማሁ ባለ ጊዜ መራራ ሐሞት መጠጣቱን የሚገልጥ ነው፡፡ ‹‹ሰተየ›› ማለት ጠጣ ማለት ነው፡፡ ሐሞት የሚለውም አሞት ተብሎ በቁሙ ይተረ ጐማል፡፡ በመዝሙር 68 ቁጥር 21 ላይ "ለመ ብሌ ሐሞት ሰጡኝ፣ ለጥማቴም ሆምጣጤ አጠጡኝ" ብሎ ነቢዩ ዳዊትን ትንቢት ያናገረ የነቢያት አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጽ ሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ "ተጠማሁ" ባለ ጊዜ ሆምጣጤ ተሞልቶበት ተቀምጦ ከነበ ረው ዕቃ ሆምጣጤውን በሰፍነግ ሞልተው ወደ አፉ አቀረቡለት፡፡ ውኃ አጠጡኝ ቢላ ቸው በሐሞት የተደባለቀ የወይን ጠጅ ሊጠጣ አቀረቡለት፡፡ ቀምሶም ሊጠጣው አልወደደም [ማቴ 27:34]፡፡ ጌታችንም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ ‹‹ተፈጸመ›› አለ፡፡ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ [ማቴ 27:48፤ ማር 15:36፤ ሉቃ 23:36፤ ዮሐ 19:29]፡፡

ቢጠጡት ለዘለዓለም የማያስጠማ ውኃ የሚሰጥ አምላክ፤ የተጠማችውን ነፍስ የሚ ያረካ ጌታ፤ ለዘለዓለም የሚፈልቅ የሕይወት ውኃ ምንጭ የሚያድል ፈጣሪ በተጠማ ጊዜ የፈጠረውን ውኃ እንኳን የሚያጠጣው የሚያቀምሰውም አላገኘም [ኢሳ 55:1]፡፡ አርባ ዓመት ሙሉ በቃዴስበረ ለነበሩ አባቶ ቻቸው ከሰማይ መና አውርዶ የመገባቸው፤ ከአለት ላይ ውኃ አመንጭቶ ያጠጣቸው ክርስቶስ በተጠማ

ጊዜ ቀዝቃዛ ውኃ ነፈ ጉት [ዘዳ 16፥1-20፤ ፩ኛቆሮ 10፡3]፡፡ የዝናማት፣ የባሕርና የውቅያኖስ ጌታ በውኃ ጥም ተቃጠለ፡፡

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሲኦል በረሃ ወድቀው በሕይወት ውሃ ጥም የተቃጠሉትን ነፍሳት ለማርካት ሲል እርሱ ተጠማ፡፡ በኃጢአት ወድቀው፣ በበደል ረክሰው፣ በነፍሳቸው ተጉሳቁለው፣ መራራ መከራን የሚቀበሉትንና ምረረ ገሃነም አፉን ከፍቶ ሆዱን አስፍቶ የሚጠብቃቸውን ሁሉ ለማዳን መራራ ሐሞትን ቀመሰ፤ ሆምጣጣ ውንም ጠጣ፡፡ የመረረውን የሰው ልጆችን ሕይወት ለማጣፈጥ የመረረውን መጠጥ ተቀበለ፡፡

5. ተቀሥፎ ዘባን (ጀርባን መገረፍ)

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጀርባው እስኪላጥ ያለ ርኅራኄ የመገረፉን ነገር የሚገልጥ ነው፡፡ "ተቀሥፎ" የሚለው ቃል ቀሠፈ-ገረፈ ካለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ነው፡፡ "ዘባን" ደግሞ ጫንቃ፣ ትከሻ፣ ጀርባ ማለት ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጠው የተገረፈ አይሰቀልም፡፡ የሚሰቀል ደግሞ አይገረፍም ነበር፡፡ ጲላጦስ ግን ኢየሱስ ክርስቶስን አስገረፈው፡፡ ከደሙ ንጹሕ ነኝ ብሎ ከታጠበ በኋላ ክርስቶስን ያለ ኃጢአቱ በመገረፍ ለአይሁድም አሳልፎ በመስጠት "ታጥቦ ጭቃ" እንዲሉ የታጠበ እጁን መልሶ አቆሸሸው [ማቴ 27፡28፤ ማር 15፡15፤ ዮሐ 19፡1]፡፡

መድኃኒታችን መንፀፈ ደይን ወድቆ በእግረ ኢጋንንት ተጠቅጥቆ በእሳት አለንጋ የሚገረፈውን የሰው ልጅ ለማዳን ሲል ጀርባውን ለግርፋት ሰጠ፡፡ ሥጋው አልቆ አጥንቱ እስኪቆጠር ተገረፈ፡፡ አይሁድ አገረ ገዥያቸው ጲላጣስ ላቀረበላቸው ምርጫ ይፈታላቸው ዘንድ ነፍሳትን ከሲኦል የሚያወጣውን ክርስቶስን ሳይሆን ራሱን እንኳን ከምድራዊ ወህኒ ማውጣት ያልቻለውን ወንበዴውን በርባንን መረጡ፡፡ መገረፍ ይገባው የነበረ በርባን ተለቀቀ፡፡ በነቢዩ በኢሳይያስ "ጀርባዬን ለገራፊዎች፣ ጉንጬንም ለጠጉር ነጪዎች ሰጠሁ" [ኢሳ 50፡6] ተብሎ እንደተነገረ ጀርባውን ለገራፊዎች አሳልፎ ሰጠ፤ ጽሕሙንም ተነጨ፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው የሰው ልጅ ከሚያድነው አምላክ ይልቅ የሚገርፈውንና የሚዘርፈውን ወንበዴመርጦ ስለ ተገኘ ነው፡፡

6. ተዐርቆተ ልብስ (ከልብስ መራቆት)

አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልብሱን መራቆቱን የሚገልጥ ነው፡፡ «ተዐርቆት» ማለት ታረዘ፤ ተራቆተ ማለት ነው፡፡ ፀሐይና ከዋክብትን ብርሃን አልብሶ የፈጠረ አምላክ ተራቆተ፡፡ ጿጋውን ለዕራቃን የሚያለብስ አምላክ ልብሱን ተገፍፎ ዕራቁቱን ቆመ፡፡ ጨለማን ለብሶ ጨለማን ተንተርሶ ይኖር የነበረውን ሰው መልሶ ብርሃን ያለብሰው ዘንድ የብርሃናት ጌታ፣ የጸጋ ሁሉ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ተገፈፈ፤ ተራቆተ፡፡

የሲኦል ወታደሮች የሆኑት ኢጋንንት የሰውን ልጅ ጸጋ ገፍፈውት ነበርና ጲላጦስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አሳልፎ በሰጣቸው ሰዓት ወታደሮች ልብሱን ገፈፉትታል [ማቴ 27፡27]፡፡ የሰው ልጅ ለቀረበለት ምርጫ የሰው ምላሽ ዘራፊው፣ ገራፊው ወንበዴ በርባን እንዲፈታለት ነበር፡፡ «አቅረ ብኩለከ እሳተ ወማየ፤ ደይ እዴከ ኀበ ዘፈቀድከ! እነሆ እሳትና ውኃን አቅርቤልሃለሁ፣ እጅህን ወደ ፈቀድከው ስደድ» ሲባል የሰው ልጅ እጁን ወደ እሳት ሰደደ፡፡

7. ርግዘተ ገቦ (ጎንን መወጋት)

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ከሰጠ በኋላ ጎኑን በስለታም ጦር መወጋቱን የሚገልጥ ነው፡፡ «ርግዘት» የሚለው ቃል ረገዘ- ወጋ ከተሰኘ የግእዝ ግሥ የወጣ ነው፡፡ ገቦ ማለት ደግሞ ጎን ማለት ነው፡፡ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ አጠገብ፣ በግራና በቀኙ ኹለት ወንበዴዎች ተሰቅለው ነበር፡፡ ሥጋቸው በሰንበት በመስቀል ላይ እንዳይኖር ጭናቸው ተሰብሮ እንዲወርዱ አይሁድ ጲላጦስን በለመኑት መሠረት ጭፍሮቹ የኹለቱን ወንበዴዎች ጭን ጭናቸውን ከሰበሩ በኋላ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ሲመጡ ፈጽሞ እንደሞተ ዐይተው ጭኑን አልሰበሩም፡፡ ነገር ግን ከጭፍሮቹ አንዱ ጎኑን በጦር ስለወጋው ወዲያው ከጎኑ ደምና ውኃ ፈሰሰ [ዮሐ 19፡33]፡፡

አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል ያደርገው ዘንድ ሞተ፤ የሰው ልጅ በዘለዓለማዊ ሞት ተይዞ ነበርና፡፡ ትልቁ ሞት በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር መለየት ነው፡፡ በጌታችን ሞት ግን ሞት ራሱ ድል ተነሣ፡፡ የሞት መውጊያ በሆነ ኃጢአት የሞተውን ሰው ለማዳን ጎኑን በጦር ተወጋ፡፡ በሰው ልቡና ተተክሎ የነበረውን ኃጢአት ከነሥሩ ነቅሎ ስለ ጣለው "ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ?" ተባለ፡፡ የሞት መውጊያው ኃጢአት ነበርና [፩ኛቆሮ 15፡4-55፤ ኢሳ 25፡8፤ ሆሴ 13፡14]፡፡

ከተወጋው የጌታችን ጎን ደምና ውኃ መፍሰሱም የእግዚአብሔርን ልጅነትና የዘለዓለምን ሕይወት አጥቶ የነበረው ሰው ልጅነቱና ሕይወቱ እንደ ተመለሰለት የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ምክንያቱም ከጎኑ በፈሰሰው ውኃ ተጠምቆ ልጅነትን፣ ደሙንም ጠጥቶ የዘለዓለም ሕይወትን ያገኛልና [ዮሐ 3፡5፤ ዮሐ 6፡54]፡፡

8. ተአሥሮ ተድኅሪት (ወደኋላ መታሠር)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኹለት እጆቹን ወደ ኋላ የፊጥኝ መታሠሩን የሚገልጥ ነው፡፡ «ተአሥሮት» የሚለው ቃል አሠረ (ሲነበብ ይላላል) ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም አሠረ ማለት ነው፡፡ "ድኅሪት" የሚለው ቃል ደግሞ ተድኅረ- ወደ ኋላ አለ ከሚለው ግሥ የወጣ ነው፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጊዜው በደረሰ ሰዓት ራሱን ለአይሁድ አሳልፎ በሰጠባት በዚያች ዕለትና ሰዓት ሻለቃውና ጭፍሮቹ የአይሁድም ሎሌዎች እጁን የኋሊት አሥረው መሬት ለመሬት ጎትተውታል፡፡ አፍገምግመውታል [ዮሐ 18፡12]፡፡

በኃጢአት ሰንሰለት የኋሊት ታሥሮ ጠላት ዲያብሎስ የሚያፍገመግመውን የሰው ልጅ ለማዳን፣ ሰውንም ከኃጢአት እሥራት ይፈታ ዘንድ ሲል መድኃኒዓለም ክርስቶስ በጠላቶቹ በአይሁድ እጅ የኋሊት ታሠረ፡፡

9. ዐምሥቱ ቅንዋተ መስቀል

መድኃኒታችን በመስቀል ላይ የተቸነከረባቸውን ጠንካራ የብረት ችንካሮች (ምስማሮች) የሚገልጥ ነው፡፡ "ቅንዋት" የሚለው ቃል ቀነወ- ቸነከረ ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ነው፡፡ መስቀል ማለት ደግሞ ዝም ብሎ የቆመ ግንድ ሳይሆን አሁን በየሥፍራው እንደምናየው ምልክት የተመሳቀለ እንጨት ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቸነከረባቸው ዐምስቱ ችንካሮች ሳዶር፣ አላዶር፣ ዳናት፣ አዴራ እና ሮዳስ ይባላሉ፡፡ እነዚህም የዐምስቱ አዕማደ ምስጢራት ምሳሌዎች መሆናቸውን አበው ያስተምራሉ፡፡

የእግዚአብሔር አብ ጸጋ፣ የእግዚአብሔር ወልድ ፍቅር፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ኅብረት በክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ያለ ጥርጥር በፍጹም ልባችን ከምናምን ምእመናን ጋር ይኹን! [፪ኛቆሮ.፲፫፥፲፬]፡፡

**በመምህር ፋሲል አስማማው**

# ክብረ ቅዱሳን



ዘክብረ ቅዱሳን ማለት የቅዱሳን ክብራቸው ፣ ለእግዚአብሔር መለየታቸው ፤በበጎ ሥራ ቸው ለሰማያዊ መንግስት በእግዚአብሔር የተመረጡ ማለት ነው ፡፡

- ቅዱስ ማለት ቀደሰ አመሰከ ፣ ለየ ፣ መረጠ ፣ አከበረ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ነው፡፡
- ቅዱሳ ማለት የተመሰገነ ሲሆን "ቅዱሳን" ማለት ደግሞ የተባረኩ የተመሰገኑ ፣ የተለዩ በብዙ ቁጥር ለወንዶች ነው ፡፡
- ቅድስት ማለት የተመሰገነች .የተባረከች ፤ የተለየች ማለት ሲሆን "ቅዱሳት" ማለት ድግሞ በብዙ ቁጥር ለሴቶች ነው ፡፡

እንደ ቅድስት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ቅድስና የባሕርይ ቅድስና እና የጸጋ ቅድስና በማለት በሁለት ይከፈላል ፡፡

**፩. የባሕርይ ቅድስና ፦**

የባሕርይ ቅድስና ገንዘብነቱ ለሕያው እግዚአብሔር ብቻ ነው ፤ የባሕርይ ቅድስና ማለት የሕያው እግዚአብሔር የባሕሪው ከማንም ያልጠሰጠው፣ ወይም ያልተቀበለው የራሱ የባሕሪው የአምላክቱ ቅድስና ማለት ነው፡፡

እግዚአብሔር በባሕርዩ ቅዱስ ስለሆነ ቅድስና ከእግዚአብሔር እግዚአብሔርም ከቅድስና ተለያይተው የማይታሰቡ ናቸው ፡፡

በሕያው እግዚአብሔር ዘንድ ከቅድስና በስተቀር እርኩሰት ፤መውቅና መነሳት ፣ሐሰት እና ንዴት የሌለበት ነው ፤ለዚህም ነው እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ ያለው ፤ ቅድስና እግዚአብሔር የባሕርዩ ፤ የአምላክነቱም መገለጫ ነው ፡፡

የሕያው እግዚአብሔርን የባሕርይ ቅድስናም ሱራፌል " ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ፀባዖት ፍፁም ምሉዕ ሰማያት ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ ፦ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች "በማለት ምሥጋና የባሕርይ ቅድስናውን ገልጸዋል፡፡ ትንቢተ ኢሳ ይያስ ፮፥፫ ራእየ ዩሐንስ 4፥8 በስፋት ስለ ሕያው እግዚአብሔር የባሕይ ቅድስና ተገልጿል፡፡

እግዚአብሔር ቅድስና የባሕርይ ገንዘቡ ነው፣ በጊዜ ሒደት ወይም በትሩፋት ያገኘው አይደለም ፡፡ለሕያው እግዚአብሔር ቅድስና ተመሳሳይ ወይንም ተወዳዳሪ የለውም፤ ቅድስናውንም ራሱ ሲናገር"እኔ እግዚአብብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝ "ይላል፡፡ ኦሪት ዘሌዋውያን 19፥2

የነቢዩ ሳሙኤል እናት ቅድስት ሐናም "እስመ አልቦ ቅዱስ ከመ እግዚአብሔር ወአልቦ ጻድቅ ከመ አምላክነ (እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለም እና ፤እንደ አምላካችንም ጻድቅ የለምና ፣ ከአንተ በቀር ቅዱስ የለም " በማለት ቅዱስ እግዚአብሔርን አመስግናለች ፤መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 2፥2 ፡፡

ሕያው እግዚአብሔር ከፍጡራን ሁሉ የከበረ በቅድስናውም ሆነ በአምላክነቱ የሚመስለው የሚተካከለው ስለሌለ ክቡር ዳዊት "መኑ ይትዔረዮ ለእግዚአብሔር በደመናት ወመኑ ይመስሎ ለእግዚአብሔር እም ደቂቀ አማልክት እግዚአ አምላከ ኃያ ላን መኑ ከማከ " (ሕያው እግዚአብሔርን በሰማይ የሚተካከለው ማን ነው ?ከአማልክትስ ልጆች እግዚአብሔርን ማን ይመስ ለዋል ? አቤቱ የሠራዊት አምላክ እንደ አንተ ያለ ማን ነው ? መዝሙረ ዳዊት 88፥6፥8

እስራኤላውያንም ከምድረ ግብጽ በወጡ ጊዜ በምስጋና መዝሙራቸው የእግዚአብሔርን የባሕርይ ቅድስና በማዘከር "መኑ ይመስለከ እምነ አማልክት እግዚአ ወመኑ ከማከ ስቡሕ በውስተ ቅዱሳን " አቤቱ በአማ ልክት መኸከል እንደ አንተ ያለ ማን ነው? በማለት በምስጋና እግዚአብሔርን አመስግ ነዋል፡፡ ኦሪት ዘጸአት 15 ፥11

ቅዱስ ዮሐንስም በራእዩ "ሁሉን የምትገዛ እግዚአብሔር ሆይ ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው ፤ አንተ ብቻ ቅዱስ ነህና " ዮሐንስ ራእይ 15፥4

ለሕያው እግዚአብሔር የባሕርይ ቅድስና ፍጹምና ታላቅ የሆነ ክብር መስጠትና መገዛት ይገባል ፤እግዚአብሔር በአምላክነቱ ክብርም ቀናዒ ነውና ፤የሕያው እግዚአብሔርን ክብር የማያውቁ እና ለእርሱ የሚገባውን ክብር ለፍጡር ወይም ለባዕድ አምልኮት በሚሰጡ ሰዎች ላይ እግዚአብሔር ይቆጣል፤ "እኔ እግዚአብሔር ነኝ ፤ስሜ ይህ ነው ፤ክብሬንም ለሌላ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም " በማለት አስጠንቅቋል ፡፡ትንቢተ ኢሳይያስ 48፥8

እነዚህን እና ሌሎች እነዚህን የመሳሰሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎችን መነሻ በማድረግ ቅድስና የባሕርይ ገንዘቡ ለሆነ ለቅዱስ እግዚአብሔር ዘወትር የምናቀርበው ምስጋና እና አምልኮት የባሕርይ አምልኮት እና ስግደት፤ ቅድስና የባሕርይው ለሆነው ለሕያው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ያስረዳናል ፡፡

**፪. የጸጋ ቅድስና**

የጸጋ ቅድስና ማለት ከእግዚአብሔር በጸጋ (በስጦታ) የተሰጠ ወይም የተገኘ ማለት ነው ፤ ከላይ እንደተገለጸው በባሕርዩ ቅዱስ የሆነው ሰማይ እና ምድርን የፈጠረ እግዚአ ብሔር ብቻ ስለሆነ የፍጡራን ሁሉ ሁሉ የቅድስና ማኛው እና ምንጩ እግዚአብ ሔር ብቻ ነው፡፡

ልዑል እግዚአብሔር በባሕርዩ ቅዱስ እንደሆነ ሁሉ የእረሰሱን አርአያ ተከትለው ሰዎችም በበጎ ሥራቸው የጸጋ ቅድስናን ያገኙ ዘንድ "ኩኑ ቅዱሳነ እስመ አነሂ ቅዱስ አነ ፦እኔ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ "በማለት በማለት የሰው ሁሉ ልጆችም የቅድስናው ተሳታፊዎች ይሆኑ ዘንድ በአባታዊ ቸርነቱ ጥሪ አቅርቧል፡፡ ዘሌ 19፥2፤

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ይህን ሲያስረዳ "ስለዚህ የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃ ችሁና በመጠን ኖራችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ የምታገኙትን ጸጋ ፈጽማችሁ ተስፋ አድርጉ ፤ እንደሚታዘዙ ልጆች ባለማወቃችሁ አስቀድሞ የኖራችሁበትን ሕይወት አትከተሉ፡፡ ዳሩ ግን እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተም ደግሞ በኑሯችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ "በማለት የፈጣሪውን ትእዛዝ እና ጥሪ ጽፏል ፩ኛ ጴጥ .1፥13—15፡፡

**በቀጣይ ኅትመት ይጠብቁ**

**በመምህርት ኑኀሚን ዋቅጅራ**

# ዜና ዕረፍት

## ክቡር ሊቀ አእላፍ ያዝዓለም ገሠሠ ከዚህ ዓለም ድካም አረፉ

በ81 ዓመታቸው መጋቢት 24 ቀን 2017 ቀን ከዚህ ዓለም ድካም ያረፉት የሊቁ ያዝ ዓለም ገሠሠ ሥርዐተ ቀብር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፥ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት፥ የመንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት የመምሪያና የድርጅት ኀላፊዎችና ሠራተኞች፥ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፥ ልጆቻቸውና ቤተሰቦቻቸው፥ ወዳጅ ዘመዶቻቸው በተገኙበት መጋቢት 25 ቀን 2017 ዓ.ም በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተፈጽሟል።

### የክቡር ሊቀ አእላፍ ያዝዓለም ገሠሠ አጭር የሕይወት ታሪክ

ክቡር ሊቀ አእላፍ ያዝዓለም ገሠሠ ከአባታቸው ከአቶ ገሠሠ ደስታና ከእናታቸው ከወ/ሮ አብችው ቦጋለ በቀድሞ አጠራር ጎንደር ክፍለ ሀገር፥ ደብረ ታቦር አውራጃ በአፈርዋ እናት ወረዳ፥ ልዩ ስሙ ደብረ ሊቃውንት ወንደ ገቲ ቅዱስ እስጢፋኖስ በሚባለው ቦታ ግንቦት 9 ቀን 1936 ዓ.ም. ተወለዱ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በተወለዱበት ደብር ወንደ ገቲ ቅዱስ እስጢፋኖስ ያገለግሉ ከነበሩ ስመ ጥር የድጓ መምህር መሪጌታ መኰንን መንፈሳዊ ትምህርት ጀምረው ከፊደል እስከ ዳዊት ከአጠኑ በኋላ፥ በቀለም አያያዛቸውና በትጋታቸው ወደፊት ለቁም ነገር የሚደርሱ መሆናቸው በመምህራቸው ግምት ስለተሰጣቸው፥ ወደ ዜማው ትምህርት ገብተው እንዲማሩ በመደረጉ ጾመ ድጓውንና የዘወትር ምዕራፉን ጠንቅቀው ዐውቀው ለዲቁና መዓርግ በቅተዋል።

ክቡር ሊቀ አእላፍ ያዝዓለም ገሠሠ ገና በሕፃንነት ዕድሜያቸው ለትምህርታቸው ያላቸውን ትጋትና የቀለም አቀባበል ስጦታ የተመለከቱ ወገኖቻቸውና መምህራን ሁሉ በትምህርት መስክ በርትተው እንዲቀጥሉበት ያበረታቱአቸው ስለነበር፤ የትውልድ ቦታቸውን ትተው ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ተለያዩ የዜማ መምህራን በመሄድ የዜማ ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ ተምረዋል።

ሊቀ አእላፍ ያዝዓለም ገሠሠ በዜማ ትምህርታቸው ቤተ ክርስቲያንን ያገለግሉ በነበረበት ወቅት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የቅኔ ትምህርት ወሳኝነት እንዳለው ስለተገነዘቡና ከመምህራንም ምክር ስለተሰጣቸው፤ ወደ ቅኔ ቤት ሄደው የቅኔውን ትምህርት ገና በልጅነት ዕድሜያቸው አጠናቅቀው ከማወቃቸውም በላይ፥ ወደ ተለያዩ የቅኔ መምህራን በመኳዝ የቅኔ ሙያን ከነአገባቡና እርባ ቅምሩ ጠንቅቀው ተምረው በመምህርነት ደረጃ ሆነው ቅኔ ያስነግሩና አንዳንድ ጊዜም በመምህራኑ ፈቃድ ለደቀ መዛሙርት ቅኔ ይዘርፉ እንደነበር ይነገርላቸዋል።

ክቡር ሊቀ አእላፍ ያዝ ዓለም ገሠሠ የቅኔውን ሙያ በየዓይነቱ ሲያወርዱት ይደነቁባቸው የነበሩት መምህራን በቅኔ መምህርነት መወሰን እንደሚገባቸው ቢመክሯቸውም፥ ለዜማው ትምህርት ከፍተኛ ጉጉት ስለነበራቸው ወደ ዜማ ቤት ተመልሰው ዜማውን እየከለሱ ሲያጠኑና በማኅሌት አገልግሎት ዜማውን ሲሉት፥ በተለይ የቅኔውን ዜማ በሚያምር የልጅነት ድምፃቸው ሲያንቆረቁሩት የሚሰሟቸው ሊቃውንት የዚህን ልጅ ፍጻሜ ለማየት ያብቃን ይሉ ነበር።

አንዳንዶች መምህራን 'በዚህ ድምፅህ የተክሌን አቋቋም ሳትዘምበት እንዳትቀር' አደራህን እያሉ ይገፋፏቸው ስለነበር የመምህራኑን ምክር በመቀበል ወደ ተክሌ አቋቋም ት/ቤት ገብተው ስመ ጥር ከነበሩት ከአለቃ መንገሻ ልጅ ከመምህር ገ/ማርያም የተክሌውን አቋቋም ለመምህርነት እስከሚበቁ ድረስ በሚገባ አጠናቀው ተምረው ተመርቀውበታል።

ክቡር ሊቀ አእላፍ ያዝዓለም ገሠሠ ሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች በሚማሩበት ወቅት ሁሉ በቤተ ክርስቲያን በሚካሄደው አገልግሎት በትጋትና በንቃት ያገለግሉ ስለነበር መምህራኑም ሆኑ የአካባቢው ሊቃውንት ልዩ ፍቅርና አክብሮት ይሰጡአቸው እንደነበር ይነገራል።

ክቡር ሊቀ አእላፍ ያዝዓለም ገሠሠ ከዚህ በላይ በተገለጸው አኳኋን የዜማውን፥ የቅኔውንና የአቋቋሙን ጥበብ በጎንደርና በበጌምድር እየተዘዋወሩ ከአጠናቀቁ በኋላ ከእርሳቸው የሚቀጽሉ ደቀ መዛሙርትን በማስከተል ወደ ጎጃም ክፍለ ሀገር ተጉዘው፥ ብዙ ሊቃውንት የሚገኙባት ዋሸራ ቅድስት ማርያምን ያስተዳድሩ ከነበሩት ከሊቁ ከመምህር ወ/ሚካኤል ዘንድ ሆነው ልዩ ልዩ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን፥ ሥርዐተ ማኅሌትንና የአደራረስ ስልቶችን አጠናክረው ተምረዋል። በተጨማሪም የጾሙን ቀለም ማለትም የቅንዋቱን ዝማሜ ከእኒሁ ስመጥር ሊቅ ከመምህር ወልደ ሚካኤል ሙያውን እስከ ይትበሃሉ ድረስ ጠንቅቀው ከማወቃቸውም በላይ በዚህችው በዋሸራ ቅድስት ማርያም በየሙያ ዘርፉ ከተሠማሩ ልዩ ልዩ መምህራን የተለያዩ ሙያዎችን በመቅሰም በቅኔው በአገባቡና በዕርባ ቅምሩ ትምህርት ጭምር ሲራቀቁበት እንደነበር የቦታው ሊቃውንት ይናገሩላቸዋል።

ክቡር ሊቀ አዕላፍ ያዝዓለም ገሠሠ በዚህ የጥናት ጊዜያቸው ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ተግተውና ነቅተው ያገለግሉ ስለነበር የዋሸራ ሊቃውንት እሳቸውን ከዚያው ለማስቀረት ይመኙ እንደነበር፥ ቃለ እግዚአብሔር ሲናገሩ የሰሙአቸው በሌሎች አድባራትና ገዳማት የሚገኙ ሊቃውንት ሁሉ በየቦታቸው ለማቆየት ያጨዋቸው እንደነበር ጓደኞቻቸውና የሚያውቋቸው ሁሉ ይናገራሉ።

ክቡር ሊቀ አእላፍ ያዝዓለም ገሠሠ ለብዙ ዘመን የደከሙበትንና የተመረ ቁበትን ያሬዳዊ ሙያ ይዘው ደቀ መዛሙርትን አስከትለው ወደ ትውልድ ቦታቸው ተመልሰው እያስተማሩና ቤተ ክርስቲያናቸውን እያገለገሉ ሳሉ፥ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ በታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጥሪ ተደርጎላቸው በ1962 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ ከተማ ገብተዋል።

አዲስ አበባ እንደመጡም በዚያ የልጅነት ዕድሜያቸው በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቻ ከሚወሰኑ ይልቅ የዘመኑን ትምህርት ቢማሩና መንፈሳ ዊውን ዕውቀት ከዘመናዊው ዕውቀት አጣምረው ቢይዙ




ለራሳቸውም ዕድገት ሆነ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚጠቅም መሆኑን ከቤተ ክርስቲያን አባቶች ምክር ስለተሰጣቸው፥ ይህንኑ ሐሳባቸውንም ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ገልጸው አባቶች ስለ አስረዱላቸው ወደ ሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ከፍተኛ ት/ቤት ገብተው እንዲማሩ ተደረገ። በዚያም ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ተምረው ቀሪውን ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት አጠናቅቀዋል።

ክቡር ሊቀ አዕላፍ ያዝዓለም ገሠሠ ትምህርታቸውን እየተማሩ ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ስለማይለዩ፥ በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስና በማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያም አብያተ ክርስቲያናት እየተገኙ ሰፊ አገልግሎት ይሰጡ ነበርና ይህንኑ አገልግሎታቸውን በመመልከት በጠቅላይ ቤተ ክህነት ተቋቁሞ ይሠራ በነበረው የካህናት ቦርድ በጸሐፊነት እንዲያ ገለግሉ ተመርጠው ለ3 ዓመታት ያህል አገልግለዋል።

በዚህ አገልግሎታቸውና በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ባላቸው የነቃ ተሳትፎ ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነት በሥራ ቢመደቡ የበለጠ እንደሚሠሩ ስለታመነበት፥ በጊዜው በነበሩ ባለሥልጣናት ሙሉ ፈቃድና ትእዛዝ ወደ መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ተዛውረው በመደበኛ ሠራተኝነት ተመድበው አገልግለዋል።

*በዚህም መደበኛ ሥራቸው፡-*

1ኛ) በበጀትና አስተዳደር መምሪያ በዋና ጸሐፊነት፥

2ኛ) በአስተዳደር ተጠባባቂ ኃላፊነት፥

3ኛ) በአስተዳደር ዋና ኃላፊነት በብቃት አገልግለዋል።

በመቀጠልም ወደ ቅርሳ ቅርስ ምዝገባና ጥበቃ መምሪያ ተዛውረው፡-

1ኛ) የቅርሳ ቅርስ ምዝገባና ጥበቃ ዋና ኀላፊ፥

2ኛ) የሥነ ጽሑፍና የቁም ጽሕፈት ኀላፊ፥

3ኛ) የጸዋትወ ዜማና የአቋቋም ትምህርት ኀላፊ፥

4ኛ) በማይክሮ ፊልምና በመሳሰሉት የሥራ ዘርፎች እየተመደቡ በቅንነትና በታማኝነት አገልግለዋል።

እንዲሁም በትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት የኅትመት ክፍል ኀላፊ ሆነው እየሠሩ እንዳሉ ወደ ሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት ዛውረው በሥራ አስኪያጅነት እንዲሠሩ በመመደባቸው ተልዕኮአቸውን ፈጽመው በውጤት ተመልሰዋል።

ክቡር ሊቀ አእላፍ ያዝዓለም ገሠሠ በየተመደቡበት የሥራ መስክ ሁሉ ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመግባባት የሚሠሩ ቅንና ታማኝ፥ የሙያ ብቃታቸው የተመሰከረላቸው በመሆናቸው ወደ ሊቃውንት ጉባኤ ተዛውረው የሥነ ጽሑፍ ምርመራ ኀላፊና የጉባኤው አባል ሆነው እንዲሠሩ ስለ ተፈቀደላቸው፥ ከሊቃውንቱ ጋር በመግባባት ከፍተኛ አገልግሎት ከመፈጸማቸውም በላይ ከጥቅምት 30 ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የሊቃውንት ጉባኤ ዋና ሰብሳቢ ሆነው እንዲሠሩ ተሹመዋል። በዚህም የሥራ ምድብ ለሥራ ባልደረቦቻቸው ለሊቃውንት ከፍተኛ አክብሮት በመስጠት በመመካከርና በመግባባት ሥራቸውን እያከናወኑ ከፍተኛ የሥራ ውጤት አስመዝግበዋል።


ክቡር ሊቀ አእላፍ ያዝዓለም ገሠሠ በቢሮአቸው ውስጥ ከሚያበረክቱት የሥራ ድርሻ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤን አደራጅታ፥ ማኅበረ ካህናትንና ማኅበረ ምእመናንን አቀናጅታ ወጥ የሆነ ሥራ በመሥራት ራሷን ለላቀ ደረጃ በማብቃት ባደረገችው ጥረት ሁሉ የበኩላቸውን ድርሻ ተወጥተዋል። በአድባራትና ገዳማት ተዘዋውረው ሰበካ ጉባኤን በማደራጀት የአብነት ት/ቤቶች እንዲጠናከሩ፥ ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋና የሰንበት ት/ቤቶች በሥርዐት እንዲደራጁ ያላሰለሰ ጥረት ከማድረጋቸው ባሻገር፤ በርቀት በሚገኙ በአስመራና በጅቡቲ አብያተ ክርስቲያናት እየተላኩ ግዳጃቸውን ተወጥተዋል። እንዲሁም ቤተ ክርስቲያናችንን በውጭው ዓለማት ከሚገኙ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር በማስተዋወቅና በውጪው ዓለም የሚታየውን የሥልጣኔ፥ የዕድገትና የልማት እንቅስቃሴ ለመጎብኘት ከሚላኩ የቤተ ክርስቲያናችን ልዑካን ጋር እየተላኩ በጀርመንና በካናዳ ሀገራት ተልኳቸውን ፈጽመው ተመልሰዋል።

ክቡር ሊቀ አእላፍ ያዝዓለም ገሠሠ ከበላይ አካል የሚሰጣቸውን የሥራ ድርሻ በቅንነት፥ በታማኝነትና በብቃት ከመወጣታቸውም በተጨማሪ፥ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ባላቸው ጽኑ ፍላጎት በማኅደረ ስብሐት ልደታ ለማርያም ደብር እየተገኙ ለብዙ ዘመናት ሰፊ አገልግሎት ያበረከቱ በመሆናቸው በሊቃውንት ጓደኞቻቸውና በማኅበረ ምእመናኑ ዘንድ ከፍተኛ አክብ

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# የቅዱስ ፓትርያርኩ ፲፪ኛ ዓመት በዓለ ሢመት በፎቶ























በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ